# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 277 ሰኔ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# «እነሱ ባልፈጸሙት ጥፋት ተረጂ ዜጎችን እርዳታ መከልከል ወንጀል ነው»

- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና
  የቀድሞው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር




**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- እነሱ ባልፈጸሙት ጥፋት ዕርዳታን ማቋረጥና ተረጂዎችን መቅጣት በሞራልም ሆነ በህግ ረገድ ተቀባይነት የሌለው ወንጀል መሆኑን የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር ገለጹ።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ከሰብዓዊ ድጋፍ ክልከላ ጋር ተያይዞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዜጎች በራሳቸው ጥፋት ሳይሆን በአገሪቱ ላይ በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን መርዳትና ከችግር መታደግ ህሊና ካለው ማንኛውም አካል የሚጠበቅ ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአሜሪካ መንግስት የሚጠበቅባቸውን እያደረጉ እንደሆነም ይታሰባል። ነገር ግን በቅርቡ በተፈጠረው ችግር ድጋፍ የሚሹ ዜጎች በራሳቸው ጥፋት ሳይሆን በሌላ ወገን ጥፋት ሌላውን አካል መቅጣት ወንጀል ነው።

አምባሳደር ጥሩነህ እንዳሉት፤ ለዜጎች የተላከ እርዳታ ለሌላ ተላልፏል እንኳን ቢባል በእነርሱ ጥፋት አይደለም። እነርሱ ሸጠውትም አይደለም። ድርጊቱ የተፈጸመው በሌላ አካል ነው ሊሆን የሚችለው። በሌላ አካል

«እነሱ ባልፈጸሙት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በከተማዋ የስርቆት ወንጀል እየተስፋፋ መምጣቱን ነዋሪዎች ተናገሩ

- ፖሊስ በበኩሉ ችግሩን ለመከላከል ስምሪቱን እንደሚያስተካክል አስታውቋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ የስርቆት ወንጀል እየተስፋፋ መምጣቱን ነዋሪዎች ተናገሩ። የስርቆት ወንጀል የሚፈጸመው የፖሊስ ስምሪት በሌለባቸው አካባቢዎች በመሆኑ ይህንን የማስተካከል ስራ እየሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ መአዛ ታደሰ በከተማዋ የዝርፊያ ወንጀል መባባሱን ለኢትዮጵያ ፕሬስ

በከተማዋ የስርቆት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ውይይቱ በሁለቱ ክልሎች መካከል ሰላምን ለማስፈን መሰረት የጣለ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የአማራና የትግራይ መስተዳድሮች ውይይት በሁለቱ ክልሎች መካከል ሰላምን ለማስፈን መሰረት የጣለ መሆኑን የአማራ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ የነበረው ጦርነት ቁሳዊ፣ ሰብአዊና ስነልቦናዊ ጉዳት አድርሷል። ከጦርነት አትራፊ ወገን የለም። የጦርነት የመጨረሻ መቋጫው የሰላም ድርድር በመሆኑ ፕሪቶሪያ ላይ

ውይይቱ በሁለቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## አራት የቀጣናው አገራት መሪዎች በሱዳን ያለውን ችግር ለመፍታት ከተፋላሚዎቹ ጋር እንዲወያዩ ተወሰነ

- ጉባኤው ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁን በዋና ፀሐፊነት በድጋሚ መርጧል

ገጽ 4
















# ለሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በጦርነቱ ለደረሰው ጉዳት መልሶ ግንባታ 20 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ግጭት ያስከተለውን ውድመት መልሶ ለመገንባት 20 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገለጸ። የኢትዮጵያ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራም ከትናንት በስቲያ ይፋ ሆኗል።

የኢትዮጵያ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራም ይፋ ሲደረግ፣ በግጭቱ 28 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ውድመትና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ የደረሰ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ ውድመቱን መልሶ ለመገንባት 20 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግም ታውቋል።

የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራሙ ይፋ በተደረገበት ወቅት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ እንደገለጹት፤ መንግስት ለፕሮግራሙ ውጤታማነት ከሚያደርገው ሰብአዊ ድጋፍ በተጨማሪ በጀት መድቦ በቁርጠኝነት እየሠራ ይገኛል።

የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ተግባር በመንግስት አቅም ብቻ የሚከናወን ተግባር ባለመሆኑ ባለድርሻ አካላትና የልማት አጋሮች ለፕሮግራሙ ስኬታማነት



የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

በፕሮግራሙ አተገባበር ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ሚኒስትሮችና በግጭት የተጎዱ ክልሎች ፕሬዚዳንቶች እንዲሁም የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪዎችና የልማት አጋሮች ኃላፊዎች በፕሮግራሙ አተገባበር ላይ ሰፊ ውይይት አድርገው የጋራ መግባባት ላይ መደረሱን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የምክክር መድረኩ ዓላማ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተካሔደው ጦርነት ሳቢያ የደረሰውን ጉዳትና መልሶ ማቋቋም የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ላይ ምክክር በማድረግ ሰው ተኮር ልማት ለማጠናከርና ማኅበራዊ ግንኙነትን ለማደስ እንደሆነ ተገልጿል።

በማኅበራዊ፣ በምርት፣ በመሰረተ ልማት፣ እና ባለብዙ ዘርፎች ላይ ጉዳት መድረሱ ተገልጾ፤ ለመልሶ ግንባታና ማቋቋም ጥረት እንደሚያስፈልግ ነው የተጠቆመው።

ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በግጭት በተጎዱ ክልሎች ተግባራዊ የሚደረግ የኢትዮጵያ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራምም ይፋ ሆኗል።

የኢትዮጵያ መንግስት በዓለም ባንክ እና የልማት አጋሮች የቴክኒክ ድጋፍ በመታገዝ ግጭቱ ያደረሰውን ውድመትና ጥፋት እንዲሁም የፈጠረውን ፍላጎት አካታች መረጃ ለመስጠት የጉዳት ፍላጎት ግምገማ ማድረጉም ተመላክቷል።



# 14 የጁስ ማምረቻ ፋብሪካዎች በጊዜያዊነት ስራ እንዲያቆሙ ተደረገ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የምርት ሂደታቸው ላይ የተለያየ ችግር የተገኘባቸው 14 የጁስ ፋብሪካዎች በጊዜያዊነት መታገዳቸውን የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን አስታወቀ።

የምግብ ደህንነት ቀን በኢትዮጵያ ለአራተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት አማካኝነት ሲከበር የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ነጋሽ ስሜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምርት ሂደታቸው ፍተሻ ከተደረገባቸው ከ15 በላይ የጁስ ማምረቻ ፋብሪካዎች መካከል 14ቱ የተለያየ አይነት የጥራት ጉድለት ስለተገኘባቸው ምርት አቁመው ችግራቸውን እንዲያስተካክሉ እየተደረገ ይገኛል።

የምርት ጥራት ጉድለት የተገኘባቸው ፋብሪካዎች በማምረቻ ቦታ አካባቢ ጽዳት ያለመጠበቅ፣ የአመራረት ጥራት ጉድለት፣ የምርት ሂደት የተመደቡ ባለሙያ ዕውቀት ማነስ፣ የፍሳሽ አወጋገድ ጉድለትና ተያያዥ ችግሮች እንዳለባቸው ተረጋግጧል ብለዋል።

ፋብሪካዎቹ ችግሮቻቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ ምርት እንዲያቆሙ ብቻ ሳይሆን ቀድሞ ያመረቷቸውና በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የጁስ ምርቶች ከገበያ እንዲሰበሰቡ ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

ምርታቸውን ከገበያ በመሰብሰቡና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንደማያደርሱ በመረጋገጡ ችግራቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ የፋብሪካዎቹን ስም መጥቀስ አስፈላጊ አለመሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር እስከ ምርት ማከፋፈል ድረስ ያለውን ሂደት በመፈተሽ ያሉባቸው ችግሮች እንዲያስተካክሉ መመሪያ የተሰጣቸው ፋብሪካዎች አብዛኛዎቹ የማስተካከያ ርምጃዎችን እየወሰዱ መሆኑን አቶ ነጋሽ ጠቁመዋል።

ምክትል ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ የጁስ ማምረቻ ፋብሪካዎቹ የቀረቡባቸው የጥራት ችግሮች ማስተካከላቸው ሲረጋገጥ ወደምርት እንዲገቡ ይደረጋል።

ባለስልጣኑ ከጁስ ምርት ባለፈ በተለያዩ 11 ምርቶች ላይ አስፈላጊውን የላብራቶሪ ምርመራ በማድረግ የጥራት ቁጥጥር ማድረጉን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ቦንሳ ባይሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ምርቶች የዜጎች ጤና ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት በመረዳት የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፤

ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ምግብ ማምረትም ሆነ ማዘጋጀት በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ኪሳራ ከፍተኛ በመሆኑ ችግሩን ለመከላከል ከምርት ግብዓት እስከ ማከፋፈያዎች ያለው ሂደት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ምግብ ጥራትና ደህንነቱን በጠበቀ ሁኔታ መመረት፣ ማከማቸትና ማጓጓዝ እንዳለበት ጠቁመው፤ ምግብ ለጤና ተስማሚ በሆነ መንገድ ብቻ መዘጋጀት እንዳለበት መገናኛ ብዙኃን በየጊዜው ግንዛቤ መፍጠር እንዳለባቸው አመላክተዋል።

# ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት ሊገጥማቸው እንደሚችል ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ሰሞኑን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች አፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። እየቀጠለ ባለው ዝናብ በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በክረምት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖርም ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደቀን የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል።

በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖራቸው እንደሚችል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ። በመሆኑም በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በክረምት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራል ብሏል።

በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱ ሲሆን፤ በአንጻሩ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖረው መጠነኛ ዝናብ በስተቀር ደረቅና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን በመግለጫው አስታውቋል።

በክረምት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራል ያለው መግለጫው፤ ይህም የግብርና ስራን ለማከናወን የአፈር ውስጥ እርጥበትን ያሻሽላል። በተጨማሪም ቀድመው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች አፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተግቢ እንደሆነ ተጠቁሟል።

በተጨማሪም የሚጠበቀው ዝናብ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል ያለው መግለጫው፤ በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተገኙት የተሻለ እርጥበት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን፣ የግጦሽ ሳር ልምላሜ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምንጮችን ለማጎልበት ያግዛል ሲል አትቷል።

ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ አዲስ አበባ፣ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና የመካከለኛው ዞኖች የጋምቤላ ክልል፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አብዛኛው ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና በተወሰኑ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ያገኛሉ።

በአንጻሩ ከኦሮሚያ ክልል ሰሜናዊ የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል የፋፈን ዞን፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ ክልል፣ አማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ ዋግኽምራ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ክልል ዞኖችና ከአፋር ክልል ዞን አምሥት በተወሰኑ ስፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

በሌላ በኩል የሶማሌ ክልል ዞኖች፣ ከደቡብ ክልል የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች ዞኖች፣ ከአፋር ክልል አብዛኛው ዞኖች ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ ብሏል መግለጫው።

ዜና


ተማሪ ሱሌይማን ዑመር


ተማሪ ጽዮን ተስፋዬ


ዶክተር አብርሃም ድሪባ


አቶ ወንደወሰን ኢየሱስወርቅ

# ለሀገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና እየተዘጋጁ መሆኑን የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ገለጹ

## - ከ869 ሺህ በላይ ተፈታኞች በበይነ መረብ ተመዝግበዋል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ለሁለተኛ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች የሚካሄደው የዘንድሮው ሀገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና በትምህርት ይዘት እና በስነልቦናም ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ኢፕድ ያነጋገራቸው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች አስታወቁ።

ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ በበኩሉ፤ በቅድመ ዝግጅት ስራው ከ869 ሺህ በላይ 12ኛ ክፍል አገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና ተፈታኞች በበይነመረብ መመዝገባቸውን አስታውቋል። ተፈታኝ ተማሪዎች በትምህርት ይዘት እና በስነልቦና ዝግጁ እንዲሆኑ ለክልሎች መመሪያ ወርዶ ተግባራዊ መሆኑም ተመላክቷል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ መድኃኒዓለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ12 ክፍል ተማሪ ሱሌይማን ዑመር ለማጠቃለያ ፈተናው ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጿል። ያጠና ተማሪ አያልፍም እድል ነው ከሚሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች በመውጣት በመተጋገዝ እና በመረዳዳት በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባም ጠቁሟል።

በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ ጽዮን ተስፋዬ በበኩሏ፣ የገባትን ለሌሎች በማስረዳት እና ሌሎች የገባቸውንም በመረዳት በቡድን እያጠናች ያላትን ዝግጅት ገልጻለች። በአብርሆት ቤተመፃህፍት በመጠቀም በፕሮግራም እያጠናችና በስነልቦናም ዝግጁ መሆኗን ገልጻለች። በፈተና ወቅት ችግር እንዳይኖርም በመንግስት በኩል አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ በወቅቱ እንዲሰራ ስትልም ጠይቃለች።

ተፈታኝ ተማሪ ንጉሱ አድማሱ በበኩሉ፣ በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ ወርክሺቶችን ከመጻህፍቶች ጋር በማገናኘት፣ ሞዴል ፈተናዎችን ደጋግሞ በማየት እየተዘጋጀ መሆኑን ገልጿል።

በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር ማስተማር ምክትል ርዕሰ መምህር አዱኛ ኢጃራ በበኩላቸው ለኢፕድ እንደገለጹት፣ በትምህርት ቤቱ ከ500 በላይ ተማሪዎች ለ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና እየተዘጋጁ ሲሆን፤ ዘንድሮ ከአምና የተሻለ ውጤት ይጠበቃል። ተማሪዎች በትምህርታዊ ጉዳዮች ኢንተርኔት እና ቤተመጻህፍት እንዲጠቀሙ፣ ያላለቁ የትምህርት ይዘቶችን እንዲያጠናቅቁ በማድረግ እገዛ እየተደረገ ነው።

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ ምክትል ፕሪንሲፓል ዶክተር አብርሃም ድሪባ በበኩላቸው፣ በ2015 የትምህርት ዘመን አገር አቀፍ ፈተና 33 ሴቶች እና 43 ወንዶች አጠቃላይ 76 ተማሪዎች በሚገባ ዝግጁ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በ2014 የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና ውጤት እንደ አገር አሳሳቢ መሆኑን በመግለጽ ነገር ግን በካምፓሱ 69 ተማሪዎች ተፈትነው 16 ተማሪዎች 600 እና ከዚያ በላይ፣ ሌሎቹ ተማሪዎች ከ400 እስከ 500 ያመጡ መሆኑን አስታውሰዋል።

መምህራንም ሞዴሎችን በማዘጋጀትና ተማሪዎች እንዲለማመዱ፣ በቡድን እንዲተጋገዙ እየተደረገ ነው። የተማሪዎችን ችግሮች በቅርበት በመከታተል አስፈላጊ የጋይዳንስ ድጋፎች ጭምር የሚደረጉ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ፤ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች አገልግሎት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ወንደወሰን ኢየሱስወርቅ በበኩላቸው፣ ተማሪዎች በትምህርት ይዘትና በስነልቦና ዝግጁ እንዲሆኑ ለክልሎች በወረደ መመሪያ መሰረት በየትምህርት ቤቶቹ ተግባራዊ መሆኑን ገልጸዋል።

የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ማጠቃለያ ፈተናዎች ቅድመ ዝግጅትም 869 ሺህ 765 ተፈታኞች በበይነመረብ ተመዝግበዋል። ከዚህም 503 ሺህ 812 ተማሪዎች የሶሻል ሳይንስ፤ 365 ሺህ 954 የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች መሆናቸውን ተናግረዋል።

የፈተና አስፈፃሚዎች፣ ሱፐርቫይዘር፣ የጣቢያ ኃላፊ ምልመላ በማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል። የፈተና አስፈጻሚዎችም ከክልሎች እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከዩኒቨርሲቲዎች በመመልመል መመሪያውን በማዘጋጀት እና ለባለድርሻ አካላት በማስተዋወቅ ለክልሎች የወረደ መሆኑንም ገልጸዋል።

የዘንድሮው የ12ክፍል አገር አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና ከሐምሌ 19 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚሰጥ ትምህርት ቢሮ ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

# በትግራይ ክልል የሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች በመጪው ዓመት ስራ ይጀምራሉ

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል በጦርነቱ ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች በመጪው መስከረም ወር 2016 ዓ.ም ስራ እንደሚጀምሩ የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን አብርሀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመጪው ዓመት በትግራይ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን ወደ መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ለማስገባት ዝግጅት እየተደረገ ነው። በዚህም በክልሉ በጦርነቱ ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች በ2016 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ ስራ ይጀምራሉ።

ዩኒቨርሲቲዎቹን ወደ ስራ ለማስገባት የትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርሲቲዎቹ ያሉበት ሁኔታ ከዩኒቨርሲቲዎቹ አመራሮች ጋር በመቀሌ ተደጋጋሚ ውይይት መደረጉንና ዩኒቨርሲቲዎቹን ስራ ለማስጀመር የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት ወደ ተግባር መግባታቸውን ዶክተር ሰለሞን ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹ የመማር ማስተማር ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የምግብ ፣የመኝታ፣እና የህክምና አገልግሎቶች ቅድሚያ የሚያሟሉበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን ገልጸው፤ ራያ ዩኒቨርሲቲም ይህንን አሟልቶ በትናንትናው እለት የተማሪዎች ምዝገባ ጀምሯል። መቀሌና አዲግራት ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በቀጣዮቹ ወራት ትምህርት መጀመር የሚያስችላቸውን ተግባር እንደሚጨርሱና ተማሪዎችን መቀበል እንደሚጀምሩ ይጠበቃል ብለዋል። አክሱም ዩኒቨርሲቲ ከሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች በበለጠ በጦርነቱ ጉዳት በማስተናገዱ የተወሰነ ጊዜ ሊዘገይ እንደሚችል ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹ የተማሪ ቅበላ ሲያደርጉ ቀድሞ ወደ ነበራቸው አቋም ባይመለሱም በመጀመሪያ መሰረታዊ የሚባሉ ነገሮች እንዲያሟሉና ሌሎች ነገሮችን ተማሪዎችን እያስተማሩ ጎን ለጎን የጎደሉ ነገሮችን እንዲያሟሉ እንደሚደረግ ገልጸዋል። በዚህም በመጪው መስከረም ዩኒቨርሲቲዎቹ መሰረታዊ ነገሮችን አሟልተው ስራ ይጀምራሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

አራቱ ዩኒቨርሲቲዎቹ ከጦርነቱ በፊት 45 ሺ ተማሪዎችን ሲያስተምሩ እንደነበር አስታውሰው፤ ከእነዚህ ውስጥም ባለፉት ዓመታት 22ሺ የሚሆኑ ተማሪዎች እንዲወጡ ተደርጎ በጊዜያዊነት ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ተመድበው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል ብለዋል።

እነዚህ ዩኒቨርሲቲዎችም አሁን ላይ ቅበላ የሚያደርጉት ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ሳይመደቡ የቆዩ 20 ሺ የሚሆኑ ተማሪዎችን ይሆናል ብለዋል።

በመጪው ሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወስደው የሚያልፉ ተማሪዎችም የዩኒቨርሲቲዎቹ ዝግጁነት ተጠንቶና ታይቶ ተማሪዎች ሊመደቡባቸው እንደሚችልም ጠቁመዋል።

ዶክተር ሰለሞን ከዚህ ቀደም በትግራይ ክልል ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩና ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ሄደው ያጠናቀቁ ተማሪዎች ውጤታቸውን የሚገልጽ የትምህርት ማስረጃ ሳያገኙ የቆዩ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን ላይ ከነበሩበት ዩኒቨርሲቲ ያገኙት ውጤት ወደ ትግራይ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲላክ አቅጣጫ መቀመጡን ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹም ውጤቱ ሲደርሳቸው የነበራቸውን ውጤት ደምረው ጥቅል ውጤታቸውን የሚገልጽ ጊዜያዊ ዲግሪ ማግኘት እንደሚችሉ ተናግረዋል።

# ዩኒቨርሲቲው በዓመት 40 የማህበረሰብ አቀፍ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረገ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በዓመት 40 የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚ ኮሌጅ የምርምር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ስለሺ አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ዘርፍ በዓመት እስከ 40 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች ቀርጾ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።

በሸክላ ስራ፣ በቀርከሀ ምርታማነት፣ በሽመና ስራ በሌሎች የዕደ ጥበብ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ የማህበረሰብ አቀፍ ፕሮጀክቶች ወደስራ መግባታቸውን ረዳት ፕሮፌሰር ስለሺ ተናግረዋል።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንዳመለከቱት፤ በጨንቻ ከተማ በቀርከሃ ፕሮጀክት ከ100 በላይ ሴቶችና ወጣቶችን በማደራጀት የተለያዩ የፈርኒቸር ውጤቶችን እንዲያመርቱ በማድረግ ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ ተደርጓል።

በአርባ ምንጭና አጎራባች አካባቢዎች የሽመና ስራ በስፋት የሚሰራ ቢሆንም፤ እስካሁን ዘርፉን ማዘመን እንዳልተቻለ አስታውሰው፤ ለሽመና ባለሙያዎች የገበያ ትስስር በመፍጠርና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው 30 የሽመና ማሽኖች ለህብረተሰቡ መቅረቡን አስታውቀዋል።

ከሸክላ ስራ ውጤቶች ጋር በተያያዘ ለሙያተኞቹ ዘመናዊ ማሽኖችንና የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት ውጤታማ እንዲሆኑ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የማህበረሰብ አቀፍ ፕሮጀክቶች የዕደ ጥበብ ውጤቶችን ማሳደግ በሚቻልባቸው መንገዶች ለአምስት ሺህ ሰዎች ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል።

በአርባምንጭ ከተማ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው የሚሰሩ 1ሺህ 600 የተለያዩ የንግድ ቤቶች እንደሚገኙ የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር ስለሺ፤ ዩኒቨርሲቲው ፍላጎት ያላቸውን የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች በመለየት የስራ ማሻሻያ ስልጠናዎች መስጠቱን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ አርባምንጭና አካባቢው በአትክልትና ፍራፍሬ የሚታወቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲው የግብርና ምርምር ማዕከላትን በመክፈት የምርምር ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በጨንቻ ከተማ የሚገኘው ግርጫ የደጋ ፍራፍሬና አትክልት የምርምር ማዕከል ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑትን የአፕልና የተለያዩ የደጋማ አትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎችን ለማህበረሰቡ እያሰራጨ መሆኑን አስታውቀዋል።

ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰብ አቀፍ ፕሮጀክቶቹ በኮንሶ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ለሚገኙ የተለያዩ የንግድና ኢንቨስትመንት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠቱን ገልጸዋል።

# አራት የቀጣናው አገራት መሪዎች በሱዳን ያለውን ችግር ለመፍታት ከተፋላሚዎቹ ጋር እንዲወያዩ ተወሰነ

## - ጉባኤው ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁን በዋና ፀሐፊነት በድጋሚ መርጧል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢጋድ የኢትዮጵያ፣ የኬንያ፣ የሶማሊያና የደቡብ ሱዳንን መሪዎች በሱዳን ያለውን ችግር ለመፍታት ከተፋላሚ ኃይሎቹ ጋር በአካል እንዲወያዩ ወሰነ። የኢጋድ ጉባኤ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ተቋሙን በዋና ፀሐፊነት ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት እንዲመሩ በድጋሚ መርጧል።

በጅቡቲ በተካሄደው 14ኛው የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) የአባል አገራቱ መሪዎች እና ባለስልጣናት በተለያዩ ቀጣናዊ ጉዳዮች እና በሱዳን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል።

በዚህም የሱዳን ወቅታዊ ሁኔታን ለመፍታት የኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያና ደቡብ ሱዳንን የአራትዮሽ ስብስብ ከጀነራል አብዱል ፋታህ አል-ቡርሃንና ከጀነራል መሐመድ ሀምዳን ዳጋሎ ጋር በቀጣይ 10 ቀናት ውስጥ በአካል እንዲወያዩ መወሰኑን የኬንያው ፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ ገልጸዋል።




አገራቱ ኢጋድን ወክለው እንደሚወያዩ እና ውይይቱ በሱዳን ተባብሶ የቀጠለውን ሁሉንም አይነት ግጭቶች ማስቆም እና ሁለቱ ወታደራዊ አመራሮች ጦርነቱን ለማቆም ቁርጠኛ አቋም እንዲወስዱ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ መሆኑን አመልክተዋል። በዚህም የዜጎችን ሕይወት ለመታደግ እንዲሁም እየወደመ ያለውን ንብረትና ሌሎች አይነት ውድመቶችን ማስቆም እንደሚቻልም ተናግረዋል።

በተያያዘም በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ከጀነራል አብዱል ፋታህ አል-ቡርሃን እና ከጀነራል መሐመድ ሀምዳን ዳጋሎ ጋር የሰብአዊ እርዳታ ኮሪደር መክፈት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ውይይት ለማድረግ ከስምምነት ላይ መደረሱን ነው የኬንያው ፕሬዚዳንት የጠቆሙት። በተጨማሪም በቀጣይ ሶስት ሳምንታት በሱዳን ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ ምክክር ሂደት ለመጀመር የመሪዎች ጉባኤው ከስምምነት ላይ መድረሱን ነው ዊሊያም ሩቶ የተናገሩት።

ኬንያ በሊቀ-መንበርነት የምትመራው የአራትዮሽ ስብስብ (ኳርቴት) በሱዳን ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት በቁርጠኝነት እንደሚሰራም ፕሬዚዳንት ሩቶ ገልጸዋል። በተጨማሪም በጉባኤው መጠናቀቂያ ላይ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እና የቀጣይ ዓመታት መሪዎች ምርጫ ተከናውኗል።

የጉባኤውን መጠናቀቅ ተከትሎ የኢጋድ አባል አገራት መሪዎች አረንጓዴ አሻራቸውን እንዳኖሩም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መረጃ ገልጸዋል።

የኢጋድ አባል አገራት "የአየር ንብረት ለውጥን አስከፊ ተጽዕኖዎች ያለማቋረጥ ተጋፍጠዋቸዋል፤ ውጤታማ የሆነ ስብሰባ ማጠናቀቃችንን ተከትሎም የአረንጓዴ ዐሻራችንን አብረን በጅቡቲ ከተማ አኑረናል" ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገልጸዋል።

በተያያዘ የኢጋድ መሪዎች ጉባኤ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ተቋሙን በዋና ፀሐፊነት ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት እንዲመሩ በድጋሚ መርጧቸዋል። "ጉባኤው ኢጋድን ለቀጣይ አራት ዓመታት እንድመራ ሙሉ እምነት ስለጣሉብኝ አመሰግናለሁ" ብለዋል ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ከተመረጡ በኋላ በሰጡት አስተያየት።

# ውይይቱ በሁለቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተደረሰው ስምምነት መሰረት ሰላም ወርዶ ህዝቡ የሰላም አየር መተንፈስ ጀምሯል። ስምምነቱ መሬት እንዲነካና ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ ካስፈለገ የሁሉም ወገኖች መልካም አስተዋጽኦ ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ግዛቸው ገለጻ፤ የሰላም ስምምነቱን መሬት ለማውረድ ሰኔ 3 ቀን 2015ዓ.ም የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድርና የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር የመሩት ልዑክ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳዎች የህዝብ ተወካዮች አባላት ባሉበት በባህር ዳር ከተማ ውይይት አድርገዋል። ዋና ዓላማው መሪዎችን ከመሪ በማገናኘት የተጀመረውን ሰላም ማጽናትና ትክክለኛ ሰላም መሬት ላይ እንዲወርድ ማስቻል ነው።

የሁለቱ ክልል ህዝቦች ለዘመናት ተዋልደውና ተጋምደው የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ወደፊትም በጋራ መኖራቸው አይቀሬ በመሆኑ የበለጠ ለማጎልበት ሰላሙን ለማዝለቅ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ማጠናከር ወሳኝ ነው ብለዋል።

በሁለቱ ክልሎች መካከል ያሉ አለመግባባቶች የህዝብን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በህግ ማዕቀፍ መፈታት አለበት። ይህም ለህዝብ ዘላቂ ሰላምና ጥቅም ሲባል የሚደረግ ግንኙነት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በውይይቱ ወቅት ለሰላም በራችን ክፍት ነው፤ ሁልጊዜም ለሰላም አማራጭ የክልሉ መንግስት ቅድሚያ ይሰጣል ሲሉ መናገራቸውን አቶ ግዛቸው ተናግረዋል።

ከዚህም ባሻገር ግንኙነቱ ከልብ መሆኑ ማስገንዘብ ተችሏል ያሉት አቶ ግዛቸው፤ ለሰላም መስፈን የትኛውንም ዋጋ መክፈል እንደሚያስፈልግ ውይይት ተደርጎበታል ብለዋል።

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳም የትግራይ ህዝብ ጦርነት የሰለቸው ህዝብ በመሆኑ የጥይት ድምጽ መስማት እንደማይፈልግ መናገራቸውን አቶ ግዛቸው ጠቁመዋል። የተጀመሩ መልካም ግንኙነቶች በየደረጃው አመራር እየተደገፉ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ወደቀድሞው ለመመለስ መግባባት ላይ የተደረሰበት ስለመሆኑም ገልጸዋል።

በትጥቅና በጠመንጃ የሚፈታ ችግር ባለመኖሩ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን በህግ፣ በውይይትና በንግግር ለመፍታት ቁርጠኝነቱ በሁለቱም ክልል አመራሮች እንዳለ መገለጹን የጠቆሙት አቶ ግዛቸው፤በሁለቱም ክልሎች በኩል በጦርነት የወደመውን ንብረት፣ መሰረተ ልማት መጠገን፣ የህዝቡን የስነ ልቦና ስብራት መመለስ፣ አካባቢውን የበለጠ ሰላም እንዲሆን ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር እንደሆነ አብራርተዋል። የተደረገው ግንኙነት የተጀመረውን ሰላም የበለጠ መሬት በማውረድ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ትልቅ መሰረት የጣለ እንደሆነም ጠቁመዋል።

አቶ ግዛቸው፤ ግንኙነቱ የመጨረሻ ሳይሆን በቀጣይ በየደረጃው ባለው አመራር ተደግፎ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይቀጥላል። ግንኙነቱን በማጠናከር በተገቢው ሁኔታ ያልተጀመሩ የየብስ የትራንስፖርት አገለግሎቶች በመደበኛነት እንዲጀመሩ፣ የንግድና የማህበራዊ እንቅስቃሴው ቀድሞ ወደነበረበት እንዲመለስ ለማድረግ በሁለቱ ክልሎች መካከል መግባባት ላይ መደረሱን ተናግረዋል።

# «እነሱ ባልፈጸሙት ጥፋት ተረጂ ዜጎችን እርዳታ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተደረገው ጥፋት ተረጂዎችን መቅጣት ደግሞ በሞራልም ሆነ በህግ ረገድ፤ በማንኛውም ሁኔታ ተገቢ ያልሆነ ነው።

መንግስታት አንዳንድ ጊዜ ለፖለቲካ ሲሉ ሌሎች መንግስታትን ለመውቀስና በእነርሱ በጥሩ እይታ ያልታየውን አካል ለመጉዳት ሲሉ የሚወስኑት ውሳኔ መኖሩን የገለጹት አምባሳደር ጥሩነህ፤ እንዲህ አይነት ውሳኔ ጥፋት ያላጠፉትን፣ የተራቡትን ዜጎች፣ በራሳቸው ጥፋት ሳይሆን በሌላ አካል ጥፋት የተጎዱትን ፣ ንብረታቸው የጠፋባቸውንና ህይወታቸው የተናጋባቸውን ሰዎች እንደገና መጉዳት በማንኛውም ሞራልም ሆነ ህግ የሚጠበቅ አይደለም ብለዋል።

በተለይም በትላልቅ አካላትና አርቀው ማሰብ ባለባቸው እንደ ተመድ አይነት አካላት ይህ መፈጸሙ ሲታይ ድርጅቱ ራሱ አሰራሩን እየተከተለ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የሰብዓዊ ድጋፍ ክልከላው፤ "አንዱ ባጠፋው በእንዲህ አይነት ሁኔታ በሚፈጸም ቅጣት ድሆች መጎዳት የለባቸውም። ቅጣት ሊደርስባቸው አይገባም" የሚል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በተለያየ ጊዜ ያወጣትንና ሌሎች ዓለም አቀፍ ህጎችን ያልተከተለ ውሳኔ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

በዚህ መንገድ ጉዳት የደረሰበት ህዝብ ባላጠፋውና በማያውቀው ምክንያት እየተቀጣ መሆኑን ድምጹን ከፍ አድርጎ ማሰማት እንዳለበትም አምባሳደር ጥሩነህ መክረዋል። "እየደረሰባቸው ያለውን ችግር ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ማሰማት አለባቸው። በዚህ ምክንያት ምን አይነት ችግር እየደረሰባቸው እንደሆነና ልጆቻቸው በምን ሁኔታ እንዳሉ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። መንግስትም ይህንኑ መግለጽ ይኖርበታል። እያደረገ ያለውንም መልካም ተግባር ማሳወቅ አለበት። የጀመረው ምርመራም በፍጥነት ክሱን ላቀረቡት አካላትም ሆነ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳወቅ አለበት።" ብለዋል።

በቅርቡ ሰብዓዊ እርዳታ ላልታለመለት ዓላማ ውሏል በሚል ክስ የዓለም ምግብ ድርጅትና የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ድጋፋቸውን ማቋረጣቸውን ተከትሎ መንግስት ውሳኔው ፖለቲካዊ ዓላማ ያለውና ፕሮፓጋንዳ ከመሆኑም በላይ ተረጂ ዜጎችን ለጉዳት የሚዳርግ እንደሆነ መግለጹ ይታወሳል።

# በከተማዋ የስርቆት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድርጅት ገልጸዋል። እርሳቸውም የዝርፊያ ወንጀል ከተፈጸመባቸው ነዋሪዎች አንዷ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ወይዘሮ መአዛ ደሳለኝ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ የስርቆት ወንጀል የደረሰባቸው በተለምዶ ፍልውሃ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መሆኑን ገልጸው፤ መኪና እያሽከረከሩ ባለበት ጊዜ ወጣቶች አስፓልት የሚሻገሩ መስለው ከመሀከላቸው አንዱ ከመኪናቸው ፊት ለፊት መውደቁንና ሌሎቹ ወጣቶች ልጁን ገጨሽው በሚል ወከባ በመፍጠር እሳቸው ተገጨ የተባለውን ልጅ ከመኪና ወርደው ሊያዩት በሄዱበት ቅጽበት ሌቦቹ የመኪናቸውን ሁለቱንም በር በመክፈት ሞባይላቸውን መውሰዳቸውን ያስታውሳሉ። ተገጨ የተባለው ልጅ ጭምር ከሌሎች ግብረ አበሮቹ ጋር አብሮ መሮጡንም ነው የተናገሩት ።

እንደ ወይዘሮ መአዛ ገለጻ፤ በወቅቱ ተደናግጠው ስለነበር ስለ መዘረፋቸው ለፖሊስ ሳያመለክቱ በቀጥታ ወደ ቤታቸው ሄደዋል። እንደዚህ ያሉ ወንጀሎች በተደጋጋሚ በብዙ ሰዎች የሚፈጸሙ እንደመሆናቸው የጸጥታ አካላት ጉዳዩን ተከታትለው ድርጊት ፈጻሚዎቹን ለህግ ሊያቀርቡ እንደሚገባም አመልክተዋል።

ሌላኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ እንዳሻው አርጋቸው ጠዋት ወደ ስራ ለመሄድ ወደ 22 ጎላጎል የሚሄድ ታክሲ ተሳፍረው እንደሄዱና ከታክሲው እንደወረዱም እሳቸው ተሳፍረውበት የነበረ ታክሲ ውስጥ የነበረች ልጅ ተዘረፍኩ እያለች ማልቀስ መጀመሯን ያስታውሳሉ። አቶ እንዳሻው እሷን በማጽናናት ላይ እያሉም ሞባይላቸውን ወደ አስቀመጡበት የእራሳቸው ኪስ ውስጥ ሲከቱ የሳቸውም ስልክ እንደሌለና በአንድ ታክሲ ሁለት ሰዎች የተዘረፉበት አጋጣሚ መኖሩን ነግረውናል።

እንደ አቶ እንዳሻው ገለጻ፤ ሰዎች በአዲስ አበባ ባገኙት ታክሲ ዘው ብሎ ከመግባት ይልቅ ታክሲው ከየት የመጣ ነው፣ አስቀድሞ ወዴት የሚሄድ ነበር የሚለውን አስበና ጠይቆ በመግባት ጥንቃቄ ሊያደረጉ ይገባል። ፖሊሶች በዚህ ጉዳይ ላይ ክትትል ማድረግ አለባቸው። ምክንያቱም ነዋሪው ከወንጀለኞች መከላከል የፖሊስ ዋነኛ ተግባር ነው።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ በከተማዋ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን ለመከላከል የአዲስ አበባ ፖሊስ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በርካታ ስራዎች እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

ፖሊስ በተለያየ ጊዜ በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች የማታለል(ሿሿ)፣ ንጥቂያና የዘረፋ ወንጀሎች እንደሚፈጸሙ በተደጋጋሚ መረጃ እንደሚደርሰው አውስተው፤ በአብዛኛውም ጊዜ ወንጀሎቹ የሚፈጸሙት የፖሊስ ስምሪት በሌለባቸው አካባቢ መሆኑን ተናግረዋል።

ኮማንደር ማርቆስ ይህንን ችግር ለመቅረፍም የፖሊሶች የስምሪት አቅጣጫ በየጊዜው እየተሻሻለ መሆኑን ገልጸዋል።

አንዳንድ ጊዜም ሰዎች ሲዘረፉ እያዩ በፍርሀት አልያም እኔ ላይ አልሆነም በሚል ሌባን እያዩ ዝም የሚሉ ሰዎች በመኖራቸው ችግሩ እንዲስፋፋ ምክንያት መሆኑን ጠቁመው፤ ሁሉም ሰው በያገባኛል መንፈስ ወንጀልን ለመከላከል ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት በርካታ ሰዎች ወንጀል እንደሚጸምባቸው ተናግረዋል። ይህንንም ለመከላከል ሰዎች ሌባ ሲዘርፍ በሚያዩበት ጊዜ እኔ ላይ አልሆነም በማለት እንዳላዩ ከማለፍ ይልቅ ለፖሊስ በማሳወቅ ወንጀልን መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል።

እንደ ኮማንደር ገለጻ ፤ሌላኛው ወንጀልን እያስፋፋው የሚገኘው ጉዳይ ሰዎች በወንጀሉ ላይ እኔም ተጠቃሚ ልሆንበት እችላለሁ በሚል የሚገቡበት አጋጣሚ አለ። በአሁኑ ጊዜም በርካቶች ገንዘብ አግኝቼ እኔም እጠቀማለሁ በሚል በርካቶች ያላቸውን ንብረት የሌባ ሰለባ እየሆኑ ይገኛል።

ኮማንደር ማርቆስ የፖሊስ ተልእኮ ወንጀል ከመፈጸሙ አስቀድሞ መከላከል እና ከተፈጸመ በኋላ ደግሞ ለህግ በማቅረብ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ ማድረግ መሆኑን አመልክተው፤ለዚህ ተልዕኮ መሳካት ዋነኛው መሳሪያ መረጃ በመሆኑ ህብረተሰቡ የወንጀል ድርጊቶችን ሲመለከት ለፖሊስ መረጃ እንዲሰጥ መልእክታቸው አስተላልፈዋል።

በአዲስ አበባ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 270 ወንጀሎችን መከላከል ቢቻልም ይህ በቂ ባለመሆኑ ፖሊስ ወንጀል የመከላከልና የመቆጣጠር ስራውን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ በኢጋድ ጥላ ስር የምትጫወተው ሚና ተጠናክሮ ይቀጥላል

የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ድርጅት በምህጻረ ቃሉ ኢጋድ እአአ በ1986 በኢትዮጵያ፤ በኬንያ፤ በሱዳን፤ በሶማሊያ፤ በጅቡቲና ኡጋንዳ አማካኝነት ተመሰረተ:: ድርጅቱ ሲመሰረት ዋነኛ ዓላማው የነበረውም በምስራቅ አፍሪካ በተደጋጋሚ እየተነሳ የበርካቶችን ህይወት የሚቀጥፈውን ድርቅንና ጦርነትን ለመግታት፤ ቀጣናውንም ሰላምና ልማት ወደ ሰፈነበት ቀጣና ለመለወጥ ነው::

ይህንኑ ዓላማ ወደ ተግባር ለመቀየርም ኢጋድ በየአባል አገራቱ በርካታ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል:: ጦርነትና አለመረጋጋት የሚስተዋልባቸውን የቀጣናውን አገራት ፊታቸውን ወደ ሰላም እንዲመልሱ የማግባባት፤ ግንዛቤ የመፍጠርና ዘላቂ ሰላም የሚገኝበትን ስልት ሲነድፍ ቆይቷል::

በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የሚስተዋለውን የትምህርት እና የጤና ተቋማት ተደራሽነት ውስንነትን ለመቅረፍ የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግም አገራቱ የተሻለ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ የበኩሉን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: ለዚህም እንደ አብነት በደቡብ ሱዳን፤ በሱዳንና በሶማሌያ ያደረጋቸው ጥረቶች ተጠቃሾች ናቸው:: አሁንም የሰሜን ሱዳን ተፋላሚዎችን ወደ ሰላም ለመመለስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ኢጋድ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነው::

በተመሳሳይ መልኩ በጎረቤት አገራት የሚነሱ አለመግባባቶች ቶሎ እንዲፈቱና አገራቱ በፍጥነት ፊታቸውን ወደ ልማት እንዲያዞሩ በማድረግ ረገድ ኢትዮጵያ እየተጫወተች ያለችው ሚና መተኪያ የሌለው ነው:: የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን በመጡ ማግስት ጀምሮ በደቡብ ሱዳን፤ በሱዳንና በሶማሊያ ወደ ግጭት የገቡ ኃይሎችን በመሸምገል ውጤታማ ተግባራትን አከናውነዋል::

ግጭት ባልቆመባቸው በሱዳን የአብዬ ግዛትና በሶማሊያ የሰላም አስከባሪ ኃይልን በመላክ ለአባል አገራቱ ጥላና ከለላ መሆን ችላለች:: ከሰሞኑም በቀውስ የምትገኘውን ሱዳንን ወደ ሰላም ለመመለስ የኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ እና ደቡብ ሱዳን መሪዎች ከጀነራል አብዱል ፋታህ አል-ቡርሃን እና ጀነራል መሐመድ ሀምዳን ዳጋሎ ጋር እንደሚወያዩ አስታውቀዋል::

ውይይቱ በሱዳን ተባብሶ የቀጠለውን ጦርነት ማስቆም፣ ሁሉም አይነት ግጭቶች እንዲቆሙ እና ወታደራዊ አመራሮቹም ጦርነቱን ለማቆም ቁርጠኛ አቋም እንዲወስዱ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ መሆኑ ተመላክቷል::

በሌላም በኩል ላለፉት አርባ ዓመታት በድርቅ የሚጠቃውን የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናን ለእርሻና ለኑሮ ተስማሚ ወደ ሆነ አካባቢ ለመቀየር ኢጋድ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል:: በዚህ ረገድ በተለይም ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለችው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ኢጋድ ያስቀመጣቸውን ዋና ዋና አላማዎች በማሳካት ረገድ ተጠቃሾች ናቸው::

ኢትዮጵያ በተለይም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በየዓመቱ በበርካታ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን በመትከል በቀጠናው የሚታየውን ድርቅ በዘላቂነት ለመቋቋም አበክራ በመስራት ላይ ትገኛለች:: ከዚያም ባሻገር የአካባቢ መራቆት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ዋነና ችግር መሆኑን በመረዳት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ከኢትዮጵያ አልፎ በኢጋድ አባል አገራት ዘንድ እንዲተገበር የመሪነት ሚናውን ወስዳ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች::

ኢትዮጵያ የቀጠናውን አገራት ልማት በማቀራረብ ረገድ እየተጫወተችው ያለችው ሚና በአካባቢ ጥበቃ ብቻ የተገታ አይደለም:: በተለይም ከአባይ ግድብና ከጊቤ ሶስት ግድቦች የሚመነጭ ኃይልን ለጎረቤት አገራት በተመጣጣኝ ዋጋ በማዳረስ ቀጠናው በኃይል እንዲተሳሰር በማድረግ ላይ ትገኛለች:: በመንገድና ባቡር መሰረተ ልማቶች ላይ እያከናወነች ያለው ተግባርም የዚህ ሌላው መገለጫ ነው::

በድርቅና ርሃብ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ዛሬ ስንዴን በማምረት ኤክስፖርት የማድረግ ደረጃ ላይ ደርሳለች:: ይህ የአካባቢውን አገራት ከማነቃቃቱም ባሻገር አባል አገራቱ በቅርበት ስንዴን እንዲያገኙ ዕድል ፈጥሮላቸዋል:: በቀጣይም ጎረቤት አገራት ከኢትዮጵያ ሩዝና መሰል ሰብሎችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት አሰራር ተዘርግቷል::

የኢጋድ አንዱ ዓላማ አባል አገራቱ የተሻለ የንግድ ልውውጥ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው:: በተለይም በአባል አገራቱ መካከል ነጻ የንግድ ቀጠናን ዕውን በማድረግ ሸቀጦች ያለምንም መሰናክል በሁሉም አገራት ገበያ እንዲገኙ ዕድል መፍጠር በኢጋድ በኩል በትኩረት እየተሰራበት ያለ ጉዳይ ነው:: ይህንኑ ዕውን ለማድረግም ኢትዮጵያ በድሬዳዋ አካባቢ ነጻ የንግድ ቀጠና ኮሪደር በመክፈት የኢጋድን አላማ ወደ መሬት ለማውረድ እየሰራች ነው::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በኢጋድ ጥላ ስር ሆና በግብርና፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሰላምና ደህንነት፣ በመሰረተ ልማት እና ሌሎችም መስኮች የማይተካ ሚናዋን እየተወጣች፤ የምስራቅ አፍሪካ አባል አገራት በልማትና በሰላም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩሏን ሚና እየተጫወተች ትገኛለች:: ይሄው ተግባሯም ኢጋድ በቀጣናው የያዘውን ግብ እንዲያሳካ የሚያግዝ እንደመሆኑ፤ ቀጣይነት ባለው መልኩ ትስስርና ትብብሩን በሚያጠናክር መልኩ ኃላፊነቷን ትወጣለች::


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ከእርዳታ አቅርቦት ስርቆት ክስ በስተጀርባ

ከመርደቂዮስ

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለውጡን ፣ የለውጡን ኃይል እና አገርን እንደአገር የሚያጠለሹ የተለያዩ ትርክቶች ተፈጥረው በዓለም አቀፍ መድረኮች ሳይቀር ሲደመጡ ተሰምተዋል። በዚህም ዓለም አቀፉ ህብረተሰብ በአገሪቱ እየተካሄደ ስላለለው ለውጥ ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኝ ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል።

በተለይም ላለፉት አራት ዓመታት በአብዛኛው የምእራቡ ዓለም መንግስታት፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ተቋማት፣ የእርዳታ ድርጅቶችና የመገናኛ ብዙሀን በስፋት በተሳተፉባቸው የአገርና የመንግስትን ገጽታ የማጠልሸት ዘመቻዎች፤ አገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንድታልፍ ተገዳለች።

እነዚህ ዘመቻዎች በዋነኛነት በተጨባጭ መረጃዎች ላይ ያልተመሰረቱ፤ የባለጉዳዩን ሕዝብና መንግስት የሚያገሉ፤ እራሳቸው ከሳሽ፣ ምስክርና ዳኛ ሆነው የሚቀርብበት፤ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ዓላማ የተሸከሙ እንደነበሩ ለመላው ሕዝባችን የተሰወሩ አልነበሩም።

ዘመቻዎቹ በአገሪቱ ሰሜን ክፍል ለሁለት ዓመታት በተደረገው የእርስ በርእስ ጦርነት ወቅት ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰው የነበር ሲሆን፣ የአገሪቱን አንድነት ጨምሮ አገረ መንግስቱን ከፍ ያለ ስጋት ውስጥ ከቶ እንደነበር አይረሳም።

በተለይም አገረ መንግስቱን በተለያዩ አጣብቂኝ ውስጥ በመጨመር የተጀመረውን ለውጥ ለማደናቀፍ የሄዱበት ርቀት ምን ያህል እንደነበር ለማንም የተሰወረ አይደለም፣ ስለራሳቸው ገለልተኝነት መሽቶ እስኪነጋ የሚደሰኩሩ፤ በሙያዊ ስብእናቸው ለራሳቸው ከፍያለ ከበሬታ የሚሰጡ ዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ሳይቀሩ የዘመቻው አካል ሆነውም ታይተዋል።

እነዚህ አካላት በተለይም የእርዳታ እህል አቅርቦቶችን በተመለከተ በጦርነቱ ወቅት ሆነ ጦርነቱ በሰላም ስምምነት ከተቋጨ በኋላ የተለያዩ ዘገባዎችን በማውጣት፤ በአገርና በመንግስት ላይ ጫናዎችን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል፤ እየተንቀሳቀሱም ነው።

በጦርነት ወቅት ስለነበረው እውነታ በርግጠኝነት እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር ገለልተኛ አካል ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የማጣራት ስራዎችን ጊዜ ወስደው መስራት እንደሚኖርባቸው ይታመናል። ከዚህ ውጪ የሚደረጉ የማጣራት ስራዎች በራሳቸው ሙሉ ሆነው መተማመንንና ተጠያቂነትን ማስፈን አይችሉም ።

በርግጥ ከጦርነቱ ቀደም ባለው ጊዜ ሆነ፤ በጦርነቱ ጊዜና በኋላ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ተቋማት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የእርዳታ አቅርቦቶችን በራሳቸው ተቋማዊ መዋቅሮች፤ ከአካባቢ አስተዳደሮች ጋር በመሆን ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

መንግስትም ካለበት ኃላፊነት በመነሳት የእርዳታ አቅርቦቶቹ ለተረጂው ህዝብ በአግባቡ መቅረባቸውን በአስተዳደር መዋቅሮቹ በኩል በጠንካራ ዲስፕሊን ለመቆጣጠር ሰፊ ጥረቶችን አድርጓል።

ጦርነቱ በሰላም ስምምነት ከተቋጨ በኋላም በጦርነቱ አካባቢዎች ሆነ በሌሎች የተለያዩ የአገሪቱ ስፍራዎች በተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ችግር ውስጥ ለወደቁ ዜጎች ለጋሽ ተቋማት የእርዳታ አቅርቦቶችን ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

የክልል እና የፌደራል መንግስታትና መላው የኢትዮጵያ ህዝብም "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚል መርህ በችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖቹ የተቻለውን ሁሉ አድርጓል፤ ዛሬም እያደረገ ነው። ካለው የመረዳዳት የቆየ ባህል አንጻር ወደፊትም ያደርጋል።

እንደ አገር ስኬታማ እየሆንበት ያለው የበጋ እርሻ ስንዴ ከፍያለ አስተዋጽኦ እንደነበረው ማስታወስም ተገቢ ነው።ይህ ደግሞ ከሁሉም በላይ መንግስት በምግብ እህል እጥረት ሊያጋትሙት የሚችሉሉ የአደጋ ተጋላጭነቶችን ለዘለቄታው ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ የእርዳታ አቅርቦቶች ህገወጥ በሆነ መንገድ ላልተገባ ተግባር ውለዋል የሚሉ ክሶች ከምዕራባውያኑ የእርዳታ ተቋማትና የመገናኛ ብዙሀኖቻቸው መደመጥ ከጀመሩም ውለው አድረዋል። ክሶቹንም ተከትሎ ያልተገቡ ውሳኔዎች ሲተላለፉ እየተስተዋለ ነው።

**አገር ከጠባቂነት ወጥታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ በምግብ እህል እራሷን ለመቻል የጀመረቻቸው ጥረቶች በዚህ መልኩ ፍሬ ማፍራት በጀመረበት ማግስት የመንግስትን ስም ባልተገባ መልኩ ለማጠልሸት የሚደረጉ ጥረቶች ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው**

የእርዳታ ተቋማቱ የእርዳታ አቅርቦቶችን ወደ ተረጂው ሕዝብ በራሳቸው አደረጃጃት እያቀረቡ ባለበት ተጨባጭ ሁኔታ፣ መንግስትን በተናጠል ለችግሩ ተጠያቂ ማድረጋቸው ግርታን የሚፈጥር ነው።

መንግስት ክሶቹን ለማጣራት ኮሚቴ አዋቅሮ ወደ ስራ እየገባ ባለበት ሁኔታ፤ ለማጣራቱ ሂደት ተአማኒነት ከኮሚቴው ጋር ተባብሮ ከመስራት ይልቅ ተገቢውን የማጣራት ሂደት ያሳለፈውን ሪፖርት ይፋ ለማድረግ መቻኮላቸው የሪፖርቱን ተአማኒነት በራሱ የሚፈጥረው ሆኗል።

በከፍተኛ የህዝብ ውክልና ወደ ስልጣን የመጣው የአገሪቱ መንግስት ፤ ከአገርና ከህዝብ የሚበልጥ አጀንዳ ፤ የፖለቲካ መሰረትም የለውም፤ እስካሁን በመጣባቸው መንገዶችም ዋነኛ አጀንዳ አድርጎ የሄደው የአገር ሉአላዊነትንና የህዝቦችን ሁለንተናዊ ደህንነት ነው።

በምግብ እራስን ለመቻል እያደረገ ያለው ሁለንተናዊ ርብርብ፤ በእርዳታ ጠባቂነት የወየበውን አገራዊ ክብር ድምቀት በመመለስ ፤ ዜጎች በልበ ሙሉነት ቀና ብለው የሚሄዱበትን ጠንካራ መንፈስና የስነልቦና መሰረት ለመጣል ነው።

ለዚህም አገርን ወደ ብልጽግና ሊወስድ የሚችል ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሪፎርሞችን በስፋት በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ከገባ ውሎ አድሯል። እያስመዘገባቸው ያሉ ውጤቶችም ተስፋ ሰጪ ከመሆን አልፈው በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና እየተሰጣቸው ነው።

ለዚህም በበጋ የስንዴ እርሻ በተገኘው ስኬት አገር በመቶ ሚሊዮን ዶላሮች ከውጪ ስታስገባው የነበረውን የስንዴ ምርት በማቆም የዓለም የስንዴ ገበያን መደባለቅ የምትችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

አገር ከጠባቂነት ወጥታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ በምግብ እህል እራሷን ለመቻል የጀመረቻቸው ጥረቶች በዚህ መልኩ ፍሬ ማፍራት በጀመረበት ማግስት የመንግስትን ስም ባልተገባ መልኩ ለማጠልሸት የሚደረጉ ጥረቶች ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው።

ጠባቂነትን በመጠየፍ ፣ ከዚህ የአገርና የህዝብን ክብር ከሚያሳንስ እውነታ አገርና ህዝብ ለመታደግ ሌት ተቀን የሚሰራን መንግስት በእርዳታ አቅርቦቶች ዙሪያ ለመክሰስ መሞከር፣ የመንግስትን ስኬቶች ለማጠልሸት ከሚደረጉ የፖለቲካ ሴራዎች ተለይቶ የሚታይም አይሆንም !።

በርግጥ ካለንበት አገራዊ ተጨባጭ እውነታ አንጻር ይህንን ክስ ሊሸከሙ የሚችሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሊኖሩ ይችላል፤ ይሕም ቢሆን መንግስትን የሚመለከታቸውን አካላት ያካተተ ጠንካራ የማጣራት ስራ የሚጠይቅ ነው።

## ተጠየቅ

# ‹‹ሙስናን ከብሔራዊ ስጋትነት ለማውረድ እየተረባረብን ነው››

- ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ
የፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር

አስቴር ኤልያስ

ሙስና ቅንቅን ነው፤ ቅንቅን ደግሞ ሰላም አይሰጥም:: ሙስናም እንዲሁ ነው፤ የአገርን ኢኮኖሚ ያቆረቁዛል:: ቅንቅን ሲያሳክክ እንጂ በውል አይስተዋልምና የሙስናም አሰራር እንዲሁ ረቂቅ በመሆኑ አገርን ገዝግዞ ለመጣል የሚያስችል አቅሙን ለማዳከም የተዘረጋውን መረብ መበጣጠስ የግድ ይላል:: ይህ ደግሞ የብዙዎችን ትብብር ይፈልጋል::

ዋናው ቁም ነገር ግን ሙስና እንዳይከሰት ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ መገንባት ነው:: ከዚህ አኳያ ሰርቶ መለወጥ የሚፈልግና ከሙስና የጸዳ ትውልድ እንዲኖረን ለማድረግ እንዲሁም በሙስና የተዘፈቀውን አካል አጣርቶ ከማቅረብና ከመከታተል አኳያ ምን እየተሰራ ነው ሲል አዲስ ዘመን የፌዴራል ሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እና የጸረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴው አባል ከሆኑት ከዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል::


ፎቶ፡- ሐዲሽ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በዚህ ዓመት ምን ጠንካራ ነገር ሰርቷል ከሚለው ጥያቄያችንን ብንጀምርስ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው:: በዋናነት የትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታ ላይ ሥልጠና በመስጠትና ለዜጎች ግንዛቤ በመፍጠር ላይ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ሙስና እንዳይከሰት አስቀድሞ መከላከል ላይ ይሰራል:: ለሙስና መከላከል ያግዛሉ ብለን የቀረጽናቸው ስትራቴጂዎች አሉ::

የሙስና ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን በሁሉም ተቋማት ላይ ማጥናት፣ መለየትና ለእሱ ደግሞ የመከላከያ ዘዴ መዘርጋት አንዱ ስራችን ነው:: ሌላው የሚሾሙ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲሁም የመንግሥት ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ካሳወቁ በኋላ ያንን ሀብት በምናረጋግጥበት ጊዜ ችግሮች ካሉ ተጠያቂ ማድረግ ሌላው ተግባር ሲሆን በዚህም እየሰራን እንገኛለን::

ሌላው ሥራችን ሙስና ከመከሰቱ በፊት ሒደት እያለ ማቋረጥ ሲሆን፣ ይህ አስቸኳይ ሙስና መከላከል ተብሎ የሚጠራ ነው:: ይህ ማለት ሙስና ሊሰራ በሒደት ላይ እያለ ከሕዝቡ ለኮሚሽኑ ጥቆማ ስለሚደርሰው ሙስናው ሳይከሰት አስቀድሞ ማቋረጥ ማለት ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ በርካታ ስራዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ሲሰሩ ቆይተዋል::

በዚህ ኮሚሽን ብቻ በዚህ ዓመት ወደ 57 የሚሆኑ ጉዳዮች ገና ከጅምራቸው በሒደት ላይ እያለ እንዲቋረጡ ተደርገዋል:: እያንዳንዳቸው ጉዳዮች በብዙ ሚሊዮን ብር ሙስና ሊሰራባቸው ያሉ ጉዳዮች በሒደት ላይ እያሉ ተቋርጠዋል::

**አዲስ ዘመን፡- ምን ማለት ነው? ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ በምሳሌነትስ ሲጠቅሱ ይችላሉ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** አስቸኳይ የተባለበት ምክንያት ሙስናው ሒደት ላይ እያለ መቋረጡ ሲሆን፣ ይህም በጥቆማ መልክ ለኮሚሽናችን የሚመጣ ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ የግዥ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ ጉዳዩ ከሙስና ጋር ንኪኪ ያለው ስለመሆኑ በሕዝቡ ጥቅማ ይደርሰንና ጥቆማው አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል የማጣራት ስራ እንሰራለን:: ሒደቱም ከመጠናቀቁና ሙስና ከመሆኑ በፊት ያቆማል:: ይህ እንግዲህ ለእኛ የተሰጠ የ45 ሰዓት ሥልጣን ነው:: ማስቆም ብቻ ሳይሆን ተቋሙ እርምጃ እንዲወስድ እናሳወቃለን:: ብሎም ጉዳዩ ወደሕግ ሔዶ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይደረጋል:: በዚህ ዓመት ብቻ በዚህ አይነት መልኩ ወደ 57 ያህል ጉዳዮችን ማቋረጥ ችለናል::

ለአብነት ያህል ጤና ሚኒስቴር በዚህ እየተጠናቀቀ ባለው በጀት ዓመት በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚገመት የአኅበር ግዥ እያካሔደ ነበር:: በዚህ የግዥ ሒደት ውስጥ አንድ የቡድን መሪ የማረጋገጫ ሰነድን በማጭበርበር ለተወዳዳሪ ድርጅት አሳልፎ በመስጠቱ ድርጅቱ አሸነፎ ነበር:: ይህ ጉዳይ ሒደት ላይ እያለ ጥቆማው ደረሰን፤ እኛም ጉዳዩን ፈተሸን፤ እንደተባለውም የማጭበርበር ስራ ስለመሆኑ አረጋገጥን:: ይህ በማጭበርበር ሊያልፍ የነበረው ወደ 30 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ነው:: ይህ ለአብነት ያነሳሁት አንድ ጉዳይ ብቻ ነው::

በመሬት በኩል ቢወሰድ በካርታ ማጭበርበር እየተከናወነ ያለ ሲሆን፣ በተመሳሳይ በሒደት ላይ እያለ እያስቆምን ነው፤ እናስቆማለንም:: ከእነዚህ 57 ጉዳዮች መካከል በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ ፍንትው ብሎ እንዲወጣና ሕዝቡም ግንዛቤ እንዲያኝም ጭምር በምርመራ ጋዜጠኝነት እያሰራን እንገኛለን::

ከሕዝብ በጣም በርከት ያሉ የሙስና ጥቆማዎች ይመጣሉ:: ከበርካታ ጥቆማ ውስጥ የሙስና ፍሬ ነገር ያለው ሆኖ ከተገኘ ለዓቃቤ ሕግ፤ ለፖሊስ ይላካል:: በእርግጥ ከሚመጣ በርካታ ጥቆማ ውስጥ ሙስና የማይሆነው ጥቂቱ ብቻ ሲሆን፣ አብዛኛው ሙስና መሆኑ እርግጥ ነው:: ከጥቂቱ ውስጥ ደግሞ አብዛኞቹ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ናቸው::

ጉዳዩን ለፍትህ ተቋማት አሳልፎ መስጠት ብቻ ሳይሆን የፍትህ ተቋማትንም ጭምር ሌላ ሙስና እንዳይፈጠር መከታተል ሁሉ በኮሚሽኑ ይሰራል::

እንደሚታወቀው ሕግ ማስከበሩ ቀደም ሲል በዚህ ኮሚሽን ሲሰራ የነበረ ነው:: ምርመራ ያለው ደግሞ ፖሊስ ዘንድ ነው:: ክስና ክርክሩ ፍትህ ሚኒስቴር ዘንድ ነው፤ ጉዳዩ በሒደት ፍርድ ቤት ድረስ ይሔዳል:: እንዲያም ሆኖ እኛ አፈጻጸሙን እንከታላለን:: ሪፖርትም እንቀበላለን:: በአገር ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ሪፖርቱን ለሚመለከታቸው እናቀርባለን:: ይህን ስናጤን አሁን በጥሩ ሁኔታ በመሰራት ላይ ይገኛል::

ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል የትውልድ ግንባታ ከመገንባት አኳያ ግን ገና ብዙ ስራ ይጠብቀናል:: ነገር ግን መስራት ካለብን ስራ አኳያ እና ካቀድነው አኳያ መልካም ነው ብለን ወስደናል::

ሌላው ተቋሙን ሪፎርም ከማድረግ አኳያ ብዙ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው:: ኮሚሽኑ አሁን ያለበትን ህንጻ አድሶ መግባት የቻለውም በዚህ ዓመት ነው:: አሁን ያለንበት ህንጻ ከመሰራቱ በፊትም ሆነ ይህ ህንጻ እያለ በዓመት ወደ 21 ሚሊዮን ብር የሚያስወጣ ወጪ ለኪራይ ይወጣ ነበር:: ይህን አሁን ማስቀረት ተችሏል::

ተቋሙ ራሱን በማዘመን ላይ ይገኛል:: እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም ያለንበት ህንጻ የታጨቀው በሀብት ምዝገባ ሰነድ ነበር:: ይህን ሰነድ ሙሉ ለሙሉ ስካን በማድረግ ዲጂታላይዝ ማድረግ ችለናል:: ይህ በጣም ጥሩ ሲሆን፣ የትኛውም ሀብት ማስመዝገብ የሚጠበቅበት ሰው የራሱን ሀብት ባለበት ሆኖ በተንቀሳቃሽ ስልኩ መመዝገብ መቻሉ ነው:: ለምሳሌ አምባሳደር ሆኖ አንድ ሰው ውደ ውጭ አገር ቢሄድ ሰነድ ለመላክ ፖስታ ፍለጋ ውጣ ውረድ ውስጥ መግባት አይጠበቅበትም:: እዛው ባለበት አገር ሆኖ ሀብቱን ማስመዝገብ ይችላል:: በእርግጥ ሰው አስቀድሞ ያለኝ ሀብት ይህ ነው ብሎ ማሳወቅ ነበረበት፤ ይሁንና ይህ ተቋም ግን ምን አለህ በማለት ሲመዘግብ ቆይቷል፤ እየመዘገበም ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የሀብት ምዝገባ ሒደቱ ዲጂታላይዝ መሆኑ ያመጣው ለውጥ አለ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ከዚህ ቀደም የነበረው ክፍተት የሚፈለገው ዳታ ሙሉ በሙሉ ለመላክ መቸገር ነበር:: በተለይም ጉዳዩን ተራ አድርጎ የማየት ነገር ይንጸባረቅ ነበር:: አሁን ዲጂታላይዝ ማድረጋችን ጥሩነቱ ለአንደኛው መጠይቅ መረጃ በአግባቡ ሞልተን እስካላጠናቀቅን ወደሌላኛው መጠይቅ መሻገር አለመቻላችን ነው፤ ስለዚህ ፎርሙ ራሱ ምላሽ እንድንሰጥ የሚያስገድድ ነው:: በዚህ ሰዓት ግለሰቡ የሚሞላውን መረጃ እያረጋገጠ ነው የሚሞላው:: በመሆኑም የሞላውን ሁሉ የሚሞላው በተጠያቂነት ነው:: በዛ አጋጣሚ የሞላው ነገር ስህተትም ከሆነ ተጠያቂ ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- ስህተት የሚሆነው እንዴት ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ለምሳሌ አንድ የራሱ የሆነን ቤት ሳያስመዘግብ ቢቀርና በእኛ የማጣራት ስራ ብናገኘው ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ተብሎ ይያዛል:: ስለዚህ የእሱ ሀብት አይሆንም ማለት ነው:: ምክያቱም በሰዓቱ ማሳወቅ ነበረበት:: ስለዚህ ይህ መሆኑ አሰራራችንን ዲጂታላይዝ በማድረጋችንም ጭምር ነው፤ ከዚህ በተጨማሪ የመረጃ ጥራት ይኖረዋል:: ሌላው ዲጂታል የመሆኑ ጥቅም ከዚህ ቀደም ሰዎች በርቀት ቦታ ላይ ነኝ ወይም ረስቼ ነው የሚሉና መሰል ምክንያችን ያስወግዳል::

በአሁኑ ወቅት እየተደረገ ያለው የመረጃ ደህንነት የበለጠ ጠንካራ እንዲሆን እያዘመንን ነው:: በሙከራ ስንሰራ የቆየን ቢሆንም አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ወደስራ እንዲገባ እያደረግን እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- የሀብት ማስመዝገብ ስራው ለዓመታት የዘለቀ ነው፤ ዋና ግቡ ሀብት ማስመዝገብ ብቻ ነው? ከዛስ በኋላ ያለው ነገር ምንድን ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ሀብት መመዝገብና ማሳወቅ መጀመሪያውኑ የእኛ ስራ አልነበረም:: መንግሥት ሕግ አውጥቷል:: ይህ ሀብት የመመዝገቡ ስራ በሰነድ ስላልነበር የምንሰራው እኛ ነን:: በአሁኑ ሰዓት ግን ምዝገባውን ወደዲጂታል ስለቀየርን የሚመለከተው ሰው የሚመዘገበው ራሱ ነው ማለት ነው:: እኛ የሚጠበቅብን ማስታወቂያ ማውጣት ነው:: አዋጁ የሚለው ሀብትህን ማሳወቅና ማስመዝገብ ነው:: ስለዚህ እኛ ደግሞ የፈጠርነው ምቹ ሁኔታ ግለሰቡ ራሱ ሀብቱን እንዲያሳውቅ ነው::

ስለዚህ የእኛ ቀጣይ ስራ የሚሆነው የተመዘገበው ሀብት ትክክል ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ማጣራት ነው:: የሙስና መከላከል ጉዳይ ቁም ነገሩ ይህ ነው:: ለምሳሌ እኔ እንደ አንድ የመንግሥት ኃላፊ የማገኘው የወር ደመወዝም ሆነ ጥቅም በግልጽ ይታወቃልና በባንክ አካውንት ውስጥ የተቆለለ ብር የሚኖረኝ ከሆነ ግን ከየት አመጣህ ሊባል ይገባል:: ዋናው የኮሚሽኑ ስራ የሚያጠራጥሩ ሀብቶች እዚህም እዚያም ሲገኙ ከየት አመጣህ? ማለት ነው:: በነገራችን ላይ አሁንም ቢሆን በዚህ የማጣራት ስራ መጠየቅ የተገባቸውን ግለሰቦች እየጠየቅን ነው:: ለፍትህ ተቋምም ክስ እንዲመሰርቱ እየላክን ነው:: እንዳጋጣሚ የራሱ ሆኖ እያለ ግለሰቡ ያላስመዘገበው ሀብት ካለም እናጣራለን:: ትክክለኛ የሆነ የራሱ ሀብት ከሆነ ደግሞ በማጣራት እንዲያስመዘግብ ይደረጋል:: ለምሳሌ በዚህ ዓመት ብቻ የ 17 ሰው አጣርተን ልከናል:: አምና ደግሞ የ 28 ሰው ልከናል::

**አዲስ ዘመን፡- ክትትላችሁ ምን ይመስላል? አጣርታችሁ የላካችኋቸው ሰዎች በአግባቡ ተጠያቂ ሆነዋል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ይህንን መጠይቅ ያለባችሁ የፍትህ አካሉን ነው:: በዚህ ዓመትም በተለይ ትኩረታችን በአመራሩ ላይ ሲሆን፣ ይህን የማጣራት ስራ አጠናክረን እንቀጥላለን:: በሒደት ደግሞ ወደሰራተኛውም የምንወርድ ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያን ሀብታቸውን በውጭ አገር ይሰውራሉ ይባላልና ይህን የምትከታተሉት እንዴት ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** በውጭ አገር ያለውም ቢሆን ጥቆማው ከደረሰን ጥናት አካሂደን ምርመራ እናደርጋለን:: ዓቃቤ ሕግ ደግሞ ባለው አሰራር መሰረት ከሚመለከታቸው ሌሎች ተቋማትና የዓለም አቀፍ ስምምነቶችንም ተጠቅሞ ሀብት የማስመለስ ስራውን ይሰራል:: የእኛ ሚና ግን እያንዳንዱ ተመዝጋቢ ሀብቱን ማሳወቅ፤ ካሳወቀ በኋላ ማረጋገጥ ላይ መስራት ነው:: በዋናነት ደግሞ ለፍትህ አካል የመረጃ ምንጭ ነን::

**አዲስ ዘመን፡- በክልል ደረጃ ያለው የሀብት ምዝገባ ምን ይመስላል? አዋጅ ያላወጡ ክልሎችም አሉና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** የሀብት ምዝገባ ሒደቱ በክልል ደረጃም በጥሩ ሒደት ላይ ይገኛል፤ በእርግጥ አዋጅ ያላወጡም ነበሩ፤ በአሁኑ ሰዓት ግን አብዛኞዎቹ እያወጡ ነው:: እስካሁንም አዲስ የተቋቋመውን ክልል ጨምሮ ማለት ነው:: ድሬዳዋ ሲጠቀም የነበረው የፌዴራሉን ነበር:: አዲስ የተቋቋሙትም አሁን ይጀምራሉ:: በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ኮሚሽኑ አዲስ ነው የተቋቋመው:: እስካሁንም ሲሰራ የነበረው በፌዴራሉ ነበር:: ከዚህ አኳያ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ተጠየቅ

# ‹‹ሙስናን ከብሔራዊ ስጋትነት ለማውረድ…

ከገጽ 6 የዞረ

የሀብት ምዝገባው በየክልሉም እየተከናወነ ይገኛል። ይህ ደግሞ ለሙስና መከላከል ጥሩ መሳሪያ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አስቀድመው እንደጠቀሱት ኮሚሽኑ የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን የለውም፤ ይህ ስራችሁን በተፈለገው ልክ ስመወጣት እንቅፋት አልፈጠረባችሁም?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** በብዙ ሰዎች ዘንድ ኮሚሽኑ የቀድሞው ሥልጣኑ ባለመኖሩ አሰራሩን ዘገምተኛ ያደርግበታል የሚል ግምት አለ፤ ይህ ግን ስህተት ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ በእንዲህ አይነት አሰራር እየሰራን ያለነው እኛ ብቻ አይደለንም። ዓለም አቀፉንም ስምምነት በማማሏት የተቋቋሙ በተለያዩ አገሮች እንደ እኛ አይነት አሰራር የሚከተሉ አሉ።

አሰራሩ ሲቋቋም በሶስት አማራጭ ነው። አንዱ ሙሉ በሙሉ በሥነ ምግባር ማስተማር፣ ማሠልጠንና ግንባታ ላይ ብሎም መከላከሉ ላይ አተኩሮ የሚሰራና ሙስናን በሲስተም የሚቆጣጠር ነው። በሲስተም የሚቆጣጠሩ በአብዛኛው የሚስተዋለው በአደጉ አገሮች ነው። ይህ ማለት እያንዳንዱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዘመናዊ የሆነበት አገር ማለት ነው። ትንሽ ከዚህ መለስ ያሉት ደግሞ መከላከሉን ይጨምሩበታል። ሕግ ማስከበሩ ግን ሁሉም ዘንድ ያለ ነው።

ማስተማሩ ላይ እየሰሩ መከላከሉ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ እንደ እኛ አይነት አሰራርን የሚከተሉ አገራት በርካታ ናቸው። እኛ ሕግ ማስከበሩንም አልተውንም። እንደማንኛውም ወንጀል የፍትህ ዘርፉ በዚህ ላይ እየሰራ ነው።

በሰው አዕምሮ ያለው ነገር ምርመራውና ክሱ ወደ ፍትህ ዘርፉ በመሄዱ ተቋሙ የተዳከመ ይመስለዋል። በሙስና መከላከል ስራ ትልቁ ጉዳይና ዘላቂ መፍትሄው የዜጎችን ሥነ ምግባር መገንባት ነው። ሌብነትና ስርቆትን የሚጠየፍ ትውልድ ላይ ገና በአግባቡ አልሰራንም። በተለይ እንደ እኛ አይነት ትልቅ አገር መስራት የሚጠበቅባት የትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታ ላይ ነው። መንግሥትም ትኩረት እንዲደረግ የሚፈልገውም ሆነ የሚያምነውም በዚህ ስራ ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እስካሁኑስ ቢሆን ትውልድ ግንባታ ላይ መስራት ያልተቻለው ለምንድን ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** በሰዎችም ሆነ በሌላው አካል ጉዳዩ ከመፈጸሙ በፊት መከላከል ላይ ያለው ትኩረት አነስተኛ ነው። በእርግጥ ሰውም የሚፈልገው ‹‹እከሌ የተባለ ግለሰብ በሙስና ወንጀል ይህን ያህል ተቀጣ›› የሚለውን ነው። ነገር ግን ዋና መፍትሔ የሚሆነው ዜጎችን በሥነ ምግባር ማነጽ ነው። እንደሚታወቀው ለኢትዮጵያውያን ይህን ማድረግ የሚከብድ አይሆንም። ምክንያቱም ባህላችንም ኃይማኖታችንም ለዚህ የሥነ ምግባር ግንባታ ስኬት ደጋፊ መሆን የሚችሉ ናቸውና ነው።

ነገር ግን በዚህ ላይ ኮሚሽኑ ብቻ ሳይሆን ዜጋውም እንደ ዜጋ አብሮ መስራት ሲገባው ኮሚሽኑ ሕግ ማስከበር አብሮ ቢሰጠው በሚል ላይ መረባረቡ ብዙ ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚል አተያይ የለኝም፤ ምክንያቱም ችግርን ማድረቅ ከምንጩ መሆን ስላለበት ነው።

ሌላው ሙስና ከተፈጸመ በኋላ ለማስቀጣትና ለመቅጣት ከመሯሯጥ ቀድሞ መከላከል ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ሙስና ከተሰራ በኋላ በወንጀል ማስጠየቁ ወጪው ብዙ ነው። ሙሰኛው የወሰደውን ገንዘብ ማስመለስ በራሱ ሙሰኛውን ለማስጠየቅ ከሚወጣ ወጪ በታች ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ቀድሞ መከላከል ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል።

በሥነ ምግባር ግንባታው ላይና መከላከሉ ላይ መስራት የግድ ይላል። በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑም ራሱ በደንብ አልሰራም። ኮሚሽኑም ሆነ ሌሎች ፍትህ ተቋማትም የሚረባረቡት መመርመሩና መክሰሱ ላይ ነው። ይህ ግን በእኔ አተያይ ስህተት ነው። ፖሊስ በአሁኑ ወቅት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያለመከሰስ መብት እንዲነሳ እያደረገ እያስከሰሰም ጭምር ነው። የምርመራ ስራውን እንዲያጠናክር ፖሊስን ማጠናከር ደግሞ ተገቢ ነው። የምርምራ ስራ በሙስና የታጀበ እንዳይሆን ፖሊሱ ራሱ በሥነ ምግባር የታነጸ እንዲሆንም ማድረግ ያስፈልጋል።



ዓቃቤ ሕጉም ክስና ክርክሩን በብቃት ለመርታት እንዲቻል ሥነ ምግባር ላይ መስራት ተገቢ ነው። ፍርድ ቤት አካባቢም የሙስናን ሁኔታ በልዩ ትክረት እንዲሰሩ ማድረግ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን በአንዳንድ ዳኞች ዘንድ የሥነ ምግባር ችግር እንዳይኖር ማድረግ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም በፖሊሱም በዓቃቤ ሕጉም ሆነ በዳኛው ዘንድ ሥልጣኑ ስላለ አንዳንዱ በሌላ አካል እጅ እንዳይጠመዘዝ ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል። ስለዚህ ማስተማሩና መከላከሉ ነው ትልቁ ጉዳይ እንጂ ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ሥልጣኑ ወደራሱ ተመልሶ ቢመጣ የተለየ ጥርስ አያወጣም። ሕግ የማስከበር ስራ ከሆነ ተልዕኮ የተሰጣቸው ተቋማት አሉና ያንን እነርሱ ያስፈጽማሉ።

ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊነትም ቢሆን በዋናነት ኮሚሽኑ ይስራው እንጂ የኃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ቤተሰብ እንዲሁም መገናኛ ብዙኃንና ሌሎች መሰል ተቋማት ሁሉ አብረው ሊረባረቡበት የተገባው ጉዳይ ነው።

መከላከል ላይ ደግሞ ትልቁን ድርሻ የሚይዙት የየተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ናቸው። የየራሳቸውን ተቋማት አሰራር በየጊዜው ማሻሻል አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር ምን ያህል ተናባችሁ እየሰራችሁ ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ብሔራዊ የጸረ ሙስና ኮሚቴ የመቋቋሙም አንዱ ምክንያት እሱ ነው። ትልቁ ጉዳይ ተቋማት ተቀናጅተው አብረው እንዲሰሩ ነው። የተዋቀሩ ተቋማት በመረጃ ልውውጥም የሚደጋገፉትም በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ናቸው። ኮሚሽኑ፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ኢንሳ፣ ፋይናንስ ደህንነት እነዚህ ተቋማት አንድ ላይ የመጡበት ዋናው ምክንያት ቅንጅት ለመፍጠር ነው። ጉዳዩ በብሔራዊ ደህንነት የተዋቀረበት ምክንያት በትኩረት መመራት ስላለበት ነው። ሙስናን ከብሔራዊ ስጋትነት ለማውረድ እየተረባረብን ነው።

የእኛ ተቋም ከፍትህና ከፖሊስ ጋር ያለው ስራ መደበኛ ነው። ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ግን የእነርሱ ሥራ ነው። ጠንካራ የምርመራ ሥራ ማካሔድን ይጠይቃል። አስተማሪ የሆነ የሕግ ማስከበር ስራ ከመስራት አኳያ ድክመት አለ። ለዚህም ነው ይህን ድክመት ለመቅረፍ ኮሚቴው ተረባርቦ የሙስና መዝገቦችንም በልዩ ሁኔታ ለማየት የሚሰራው።

**አዲስ ዘመን፡- ቅንጅቱን የፈጠሩት ትልልቅ ተቋማት ናችሁና የተመዘገበ ውጤት ይኖር ይሆን?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** የተመዘገበ ውጤት አለ። አንደኛ የስድስት ወር ሪፖርቱም እንደሚያሳየው በአገር አቀፍም በክልልም ደረጃ በርካታ የምርመራ ሥራ ተሰርቷል። እየተሰራም ነው። ሌላው ደግሞ ብዙ መዝገብም ተዘጋጅቶ ክስ ተጀምሯል። የተወሰኑትንም ወደማስቀጣት እየተደረሰ ነው። አሁን በተጀመረው ሒደት ተጠናክሮ ከቀጠለ በአገር አቀፍ ደረጃ በጣም ብዙ ጉዳዮችን መቆጣጠር ይቻላል የሚል እምነት አለኝ። ይህ አሰራር አገሪቱ የተለያዩ ፈተናዎች እያሉባት ለመስራት መሞከር በራሱ ትልቅ ተነሳሽነት ነው። እንዲያውም በዚህ አጋጣሚ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ሳላመሰግን ማለፍ አልፈልግም። ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖ ሕዝቡም ንቅናቄ የፈጠረበት ጉዳይ ሆኗልና።

**አዲስ ዘመን፡- እንደዛም ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔርንና ኃይማኖትን መሰረት አድርገው የሚፈጸሙ ሙስናዎች አሉ፤ ይህን ከመከላከል አኳያስ ምን እየተሰራ ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ሙስናን ወደብሔርና ኃይማኖት የማጣጋቱ ምስጢር በደንብ ግልጽ መሆን ያለበት ይመስለኛል። ይህ ሙሰኞች የሚፈጥሩት ስልት ነው። ሌባ ብሔርም ኃይማኖትም የለውም። የሚሰርቀው ግለሰብ ነው። ከሰረቀ በኋላ የዚህ ብሔር፤ የዚያኛው ኃይማኖት ብሎ ነገር መኖር የለበትም። ሙስና ሰርቶ በየመንደሩ መደበቅም አይቻልም።

የሙሰኛ ብልጠቱ የሚሰርቀው መውጫውን አዘጋጅቶ ነው። ቢያዝ እንኳ ለማምለጥ የሚያመቸውን ሰበብና ምክንያት አዘጋጅቶ ነው። ሲፈልገው ስርቆቱን እንዳልተፈጠረ ለማስመሰል ከፖለቲካው ጋር ያያይዛል። ግለሰቡ የሙስና ወንጀል መፈጸሙ በማስረጃ ከተረጋገጠ ከየትኛውም ኃይማኖት ይሁን ብሔር አሊያም የፖለቲካ ፓርቲ ቢሆን ስለፈጸመው ወንጀል ይጠየቃል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁኑ አሁን መብትን ወይም አገልግሎትን በገንዘብ እስከመግዛት ተደርሷል፤ ይህስ እስከመቼ ይዘልቃል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** መብትን በገንዘብ መግዛት ለተባለው በአንድ በኩል የሕዝብን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ መስራትን ይጠይቃል። መብት በገንዘብ መግዛት የለበትም። አልገዛም ብሎ መከራከርም አንድ ጉዳይ ነው። ተቋማትም ትክክለኛ አገልግሎት ለመስጠት በቁርጠኝነት መስራት አለባቸው። መብት ገዥም ሆነ ሻጭ ያልተገባውን አካሔድ ለማስተካከል ኃላፊነት አለባቸው።

ይህን ለማስተካከል በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃንም ሥልጠና ጀምረናል። በዚህም ግንዛቤ እየፈጠርን ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም የሚደርሱን ጥቆማዎች አሉ። በተለይ ደግሞ የሙስና መቀበያችንን ዲጂታል አድርገናል። የትኛውም አካል የትኛውም ስፍራ ሆኖ ያልተገባ ቅብብልን የሚያይ ከሆነ እዛው ፎቶ አንስቶም ሆነ ድምጽ ቀርጾ ሊልክልን ይችላል።

ምንም እንኳ ሁሉም የስልክ ተጠቃሚ ነው ማለት ባያስደፍረንም ጥቂት የማይባል የኢትዮጵያ ሕዝብ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ነውና ያንን ለማድረግ ብዙም አይከብድም። ነገር ግን ይህ ብቻውን መፍትሔ ነው ለማለት ሳይሆን አንድ አማራጭ ነው። ሌሎች የማህበራዊ ትስስር ገጾች ሁሉ መኖራቸው የሚዘነጋ አይሆንም ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት ብዙዎች ሙስና ሲጠየቁ እየቀረጹ ሐቁ እንዲወጣላቸው ማስረጃቸውን እያደረሱን ነው። ከዚህም የተነሳ በርካታ ርምጃ በመወሰድ ላይ ነው። መረጃውን በሚሰጡን ላይ ደግሞ አንዳች ስጋት አይደርስባቸውም። ተገቢ የሆነ ጥበቃ ይደረጋል። ስለዚህ መብትን ወይም አገልግሎትን በገንዘብ መሸጥም ሆነ መግዛት ይሉት አባዜ ከዚህ በኋላ ከባድ የሚሆን ነው። የምናጋልጠውም በቀጥታ ነው። ለዚህ ማስተማሪያ የሚሆኑ ትምህርትም በመጠናቀቁም ከሰሞኑ በሚዲያ ለመልቀቅ ተዘጋጅተናል።

ሌላው ቀርቶ ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ተሰጥቶት በውጭ አገር ያለ ዜጋችንም ያልተገባ ስራ ሲሰራ ቢገኝ እንዲሁ በተፈጠረው ፕላትፎርም ይላክልናል። በዚህ ወቅት የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚው ቁጥር ወደ 40 በመቶ ያሻቀበ በመሆኑ መረጃ ለመቀባበሉ ብዙም የምንቸገር አይመስለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- በየተቋሙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች መቋቋማቸው ይታወቃል፤ ይሁንና አንዳንዴ ያሉበት ተቋም አመራሮች ነጻ ሆነው እንዳይሰሩ የሚገድቧቸው ጊዜ እንዳለ ይነገራልና በጸረ ሙስና ትግሉ ምን ያመጣው ፋይዳ አለ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** እዚህ ላይ ጥሩ ነገሩ የሕግ ማዕቀፍ አለ፤ ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ ይፈለጋል። እነዚህ አካላት በየተቋማቱ ያስቀመጥናቸው ትንንሽ ኮሚሽኖች ናቸው ማለት ነው። በጥያቄ መልክ ያነሳሽው ጉዳይ መኖሩ ትክልል ነው። የጸረ ሙስና ትግል አመራሩን የትግሉ አካል ሳይደረግ የሚመራ አይደለም።

አንዳንድ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ያለተቋሙ አመራር የሚሄድ አይደለም። አንዳንድ ክፍሎች ግን ራሳቸውን የተቋሙ ተቆጣጣሪ አድርገው ተቀምጠዋል። ይህ ግን ስህተት ነው፤ ስራቸው ምንድን ከተባለ ተጠሪነታቸው ለአመራሩ ነው። አመራሩን ማገዝ ማማከር ነው። እነሱ እያሰቡ ያሉት የድሮውን ሕግ ማስከበሩን ነው። ሥራው መሆን ያለበት ሥነ ምግባርን በተመለከተ ሰራተኞች ሥልጠና መስጠት፣ ሀብታቸውን እንዲያሳውቁ ማድረግ፣ አመራሩን ማማከርና ስጋት የሆኑ ሙስናዎችም የት የት ላይ ነው ያሉት? በሚል ማጥናት ነው። ካጠኑ በኋላ ለአመራሩ ያቀርባሉ። ሥነ ምግባራቸው የተጓደለ አመራሮች ካሉ ጥቆማ ያደርጋሉ። ዋናው ግን ማሰልጠንና ክትትል ማድረግ ነው።

ነገር ግን አንዳንዶቹ እየሰሩ ያሉት በዚህ አግባብ አይደለም። እንደማስፈራሪያ የሚጠቀሙ አሉ። ይህን አካሄዳቸውን በየጊዜው እያረምን ነው። በሚፈለገው ደረጃ በአግባቡ እየሰሩ ያሉ መኖራቸው ደግሞ አይካድም፤ ከዚህ አኳያ በስራቸው የሚሸለሙ አሉ። አመራሩንና ሠራተኛውን የጸረ ሙስናው ትግል አጋር ማድረግ አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ትራንስፓራንሲ ኢንተርናሽናል ኢንስቲትዩትም ሆነ ሌላው ዓለም አቀፍ ተቋም ኢትዮጵያን ከሙስና አኳያ የሚያስቀምጣት ደረጃ ይመጥናታል ይላሉ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንደሌላው አገር ግምት ነው የሚያስቀምጠው። በተለይም የኅበረተሰቡን እይታ ነው የሚያስቀምጠው። ይህ ደግሞ እውነታ ላይሆን ይችላል። እሱ መረጃ እንደወረደ መወሰድ የለበትም፤ ሰውን የሚያሳስት ነው። በተለይ በታዳጊ አገራት ጦርነቱ፣ የኑሮ ወድነቱም ጭምር ስላለ እንደማንኛው ዓለምአቀፍ ተነሳሽነት እንዳለው አካል አጥንቶ የራሱን ግምት ያስቀምጣል። ለምሳሌ አንድ ሰው በኢትዮጵያ ስላለ ሙስና በሚጠይቅበት ጊዜ ያ ሰው በተለያዩ የኑሮ ውድነትና በሌላም ነገር ውስጡ ተይዞ ስለሚሆን ‹‹ሁሉም ሙሰኛ ነው›› የሚል ምላሽ ሊሰጥ ይችላል።…

**አዲስ ዘመን፡- …ነገር ግን ይህ ጥናቱ በሰዎች ሳይ ተመስርቶ የሚቀርብ ነውና እንዴት ልክ ሳይሆን ይችላል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** …ሙስና ማለት ወንጀል ነው፤ ትክክለኛ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ተጠያቂው አካል ‹‹ሁሉም ሙሰኛ ነው›› ብሎ የሚናገረው ነገር የሚሆነው አሉባልታ ነው። ስለዚህ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ነገር ግን አመላካች መሆኑ አይካድም። ምክንያቱም ሕዝቡ በዛ ልክ ተማርሮ ለምን ይናገራል የሚለው ሲስተዋል አንዳች ነገር እንዳለ ጠቋሚ ነው ማለት ይቻላል።

ነገር ግን በህዝቡ የሚነገረውን መረጃ እኛም አንንቅም። እኛም ከዚህ በኋላ የሕዝቡን አመለካከት እናጠናለን። አስቀድሜ የጠቀስኩት በተንቀሳቃሽ ስልኩ ሕዝቡ ያለው እውነታ እንዲያሳውቀን ሁሉ መደላድል ፈጥረናል። አገራችን ከሙስና የጸዳች ከሆነች የኢንቨስትመንት ፍሰትም በዛው ልክ የሚጨምር ይሆናል። ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትም መልካም የሆነ ነገር ለማድረግ ሲፈልጉ እንደዚህ አይነቶችን መረጃዎች ይመለከታሉና ከሙስና የጸዳች አገር እንድትኖረን ማድረግ የሁላችንም ድርሻ ነው።

ኮሚሽኑ ግን በቀጣይ የትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታ ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ይህን የሚያከናውነውን ከሕዝቡ ጋር በመሆን ነው። መከላከል ላይም እንዲሁ በጥልቀት አጠናክረን የምንሔድበት ይሆናል። የሀብት ምንጭን ደግሞ በጥልቀት ወደማጣራት ስራ እንገባለን። በየጊዜው የምንደርስበትን መረጃ ደግሞ ለሕዝቡ ይፋ እናደርጋለን። በተለይ የትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታና ብሔራዊ የጸረ ሙስና ፖሊሲ እየተጠናቀቀ በመሆኑ ተግባራዊ እናደርገዋለን። የሚሻሻሉ ሕጎችና መመሪያዎችም አሉና እሱን ተግባራዊ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## የቄሳርን ለቄሳር!

**ሶሎሞን በየነ**

ኮንፊሺየስ ከክርስቶስ ልደት በፊት 551 እስከ 479 ዓመተ ዓለም የኖረ የቻይና ፈላስፋ፣ መምህር እና ፖለቲከኛ ነው። የዚህ ሰው የፖለቲካ አስተምሮ " በአንድ አገር ሰላም እንዲሰፍን፣ እድገትና ልማት እንዲመጣ ሁሉም መክሊቱን አውቆ በመክሊቱ ጠንክሮ ሊሰራ ይገባል " በሚል ጽኑ መሰረት ላይ የተዋቀረ ነው።

ይሄ የፖለቲካ አስተሳሰብ ዛሬ ላይ አጠቃላይ በሆነው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ቀርቶ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባት የአባትነትን፣ ሚስት የሚስትነትን፣ ልጅ የልጅነትን፤ ሌላውም በቤተሰብ ውስጥ ያለ አካል እንደተዋረዱ የሚገባውን ቦታ ይዞ በኃላፊነት ካልተንቀሳቀሰ በቤተሰቡ ውስጥ ሰላም፣ ፍቅር፣ ተድላ አይኖርም። ችግሩ እልፍ ሲልም ቤተሰቡን ሊበትን የሚችል ነው።

በቤተሰብ ፍቅር፣ እንክብካቤና ቁጥጥር በሥርዓትና በወግ ተኮትኩቶ ያላደገ ልጅ ደግሞ ነገ ላይ ከራሱ አልፎ ለአገርና ለህዝብ ይጠቅማል ተብሎ አይታሰብም፣ ከዚህ ቤተሰብ ነገ አገርና ህዝብን የሚጠቅም ትውልድ ይወጣል ብሎ ማሰብም ያልዘሩትን እንደማጨድ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ከዚህ የተነሳ መክሊትን አውቆ መክሊትን በኃላፊነት መንፈስ በአግባቡ የመወጣቱ እውነታ አይደለም አገር፤ ቤተሰብ እንደቤተሰብ አቅም አግኝቶ ለአገር የሚጠቅም ትውልድ እንዲያፈራ ትልቅ አቅም ነው። ነገዎች ላይ ሆና ለምናስባት የበለፀገች አገር ምስረታም ዋነኛ መሰረት ነው።

ዜጎች በመክሊታቸው በሥራ ላይ ያለመሰማራታቸው ጉዳይ፤ ላለፉት ስድስት አስርታት በአገራችን ለተፈጠሩና አሁንም ዋጋ እያስከፈሉን ላሉ ችግሮች እና ችግሮቹ እየፈጠሩት ላለው ውጥንቅጥ መንስኤው እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል።

በአገሪቱ ብዛት ያላቸው ዜጎች በመክሊታቸው በኃላፊነት መንፈስ እራሳቸውን፣ ማህበረሰባቸውንና አገራቸውን በታማኝነት ከማገልገል ይልቅ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ያለቦታቸውና መክሊታቸው ተሰማርተው ፍሬ ቢስ ሲሆኑ ማየት የተለመደና ትኩረት የተነፈገ ጉዳይ ነው።

ለአብነት በጥሩ ሥነ-ምግባር ቀርፆና አስተምሮ ተማሪዎችን ለውጤት ማብቃት ለመምህር የተሰጠ መክሊት ነው። አንዳንድ መምህራን በተሰጣቸው መክሊት ጠንክረው ሠርተው ተማሪዎቻቸውን ለፍሬ ማብቃት ሲገባቸው፤ በተለያዩ አስገዳጅ ችግሮች ያለመክሊታቸው ሲደክሙ ማየት፤ በተለይም በአገራዊ ፖለቲካ ጉዳይ ተጠልፈው ሲዳክሩ ማየት ከተለመደ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ይህም በአገሪቱ የትምህርት ጥራት ላይ ለተፈጠረው ችግር እንደ አንድ ምክንያት ሊቆጠር የሚችል ነው። መምህራኑ የተማሪዎችን እውቀትና ውጤት ከማሻሻል ጀምሮ እራሳቸውን ለማብቃት የሚያስችል መነቃቃት በማጣታቸው፤ የተማሪዎች ውጤት ሆነ፤ የትምህርት ጥራቱ ከፍያለ አገራዊ አደጋ ውስጥ ወድቋል።

ለዚህ ደግሞ ባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች ውስጥ ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤት ያስመዘገቡት ሦስት በመቶዎቹ ብቻ መሆናቸው ችግሩ የቱን ያህል የገነገነ ስለመሆኑ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

በተመሳሳይ የኃይማኖት አባቶችና መምህራን ጉዳይ ብንወስድ፤ ምዕመናንን በኃይማኖት እና በስነ-ምግባር አስተምህሮዎች በመቅረጽ፤ በእምነቱ የጸና፣ ፈሪሃ እግዚኣብሔር ያለው፣ ከሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች እህትና ወንድሞቹ ጋር ተከባብሮና ተቻችሎ እንዲኖር ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር።

ነገር ግን መሬት ላይ ያለው እውነታ የተገላቢጦሽ እየሆነ ነው፤ አንዳንድ የኃይማኖት አባቶች ከተሰጣቸው መንፈሳዊ ኃላፊነት ወጥተው በተለያዩ የፖለቲካ እሳቤዎች ተጠልፈው፤ ምዕመናን በምዕመናን ላይ ሲያስነሱ፣ የተሰጣቸውን መክሊት የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ ሲያደርጉ ይታያል። በዚህም አገር እየታመሰች፤ ምዕመኑም ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል እየተገደደ ነው።

የኃይማኖት አባቶች በተሰጣቸው መንፈሳዊ ኃላፊነት ወጥተው ወርደው ባለማትረፋቸው፤ ፈጣሪውን የሚፈራ፣ ወግና ባህሉን ያልለቀቀ፣ ፍትህን የማያዛባ ህዝብ ያለባት ምድር ተብላ በዓለም ላይ የምትታወቀው ኢትዮጵያ፤ ዛሬ ላይ ወንድም ወንድሙን የሚያሳድድባት፣ ቀማኛና ወንበዴ የበዛበት፣ ሰው ተዘቅዝቆ የሚሰቀልበትና የሚቃጠልባት፣ የአንድ አገር ዜጎች ጽንፍና ጽንፍ ቁመው እርስ በእርስ ጦርነት የሚያካሂዱበት አገር ሆናለች።

ለዋቢነት ትውልድ የሚቀረጽባቸው ትምህርት ቤቶች እና ህዝብ በመንፈሳዊ ሕግ የሚመራበትን የቤተ እምነቶችን ጉዳይ አነሳን እንጂ፤ በሌሎች የሙያ መስኮች (በጤና፣ ግብርና፣ ፍልስፍና፣ ምህንድስና፣ ፖለቲካ ወዘተ.) የተሰማራው አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በተመሳሳይ በተሰማራበት የሙያ መስክ ጠንክሮ ሠርቶ አገርና ህዝብን ለእድገትና ብልጽግና ለማብቃት በሙላት ሲታትር አይስተዋልም።

በተለይ ዛሬ ላይ የማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን በቀላሉና በፍጥነት ከማሰራጨት አንጻር ቴክኖሎጂው ይዞት የመጣውን እድል እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሁሉም የፖለቲካ ተንታኝ የመሆኑ እውነታ በኛ አገር የፖለቲካ አውድ ውስጥ ይዞት የመጣው አደጋ የከፋ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ነገ ላይ የበለጸገች አገር ለመፍጠር ከሁሉም በላይ ዛሬ ላይ አርሶ አደሩ ስለ ግብርናው፣ ሃኪሙ የህብረተሰቡን ጤና ስለሚያሻሽሉ ጽንስ ሃሳቦች፣ መምህሩ መማር ማስተማሩ ስለሚሻሻልበት፣ የኃይማኖት አባቶች የእምነቱን አስተምሮ ለምዕመኑ ከማስተማር በዘለለ ስለአገር ሰላምና ህዝብ ደህንነት መጸለይ እንደሚገባቸው ይጠበቃል።

ለአገር ብልጽግና ሁሉም የተሰማራበት ሙሥክ ስለሚያድግበትና ስለሚሻሻልበት መንገድ ማሰብ፣ ማቀድና መፈፀም እንደሚኖርበት ይታመናል። ነገር ግን አርሶ አደሩ፣ ሃኪሙ፣ መምህሩ፣ የኃይማኖት አባት፣ ተማሪው፣ በጥቅሉ ከሊቅ እስከደቂቅ በማህበራዊ ሚዲያ ሁሉም ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ የሚዳክር፣ መሽቶ እስኪነጋ አጀንዳው ፖለቲካ ከሆነ አገር አገር የመሆኗ እውነታ ተጠየቅ ውስጥ የሚገባ ይሆናል።

እዚህ ላይ ስለማህበራዊ ሚዲያ ሳነሳ፤ ለአገር ዕድገትና ብልጽግና፤ ለህዝቦች ነጻነትና ፍትህ ተብለው የሚቀርቡ ጽሁፎች ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እንደሆኑ ይሰማኛል። በተለይ እንደኛ ባሉ ያደሩና የዋሉ አጀንዳዎች ላሉባቸው ህዝቦች የሚቀርቡ ጽሁፎች ተጨማሪ የችግሮቻችን ምንጮች እንዳይሆኑ አብዝቶ ማሰብ ተገቢ ነው። በመሆኑም የሚቀርቡ መረጃዎች ለአንባቢው በትክክለኛ መረጃ እና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል።

በአገራችን ባለው አሁነኛ እውነታ ግን ህዝብን በህዝብ ላይ የሚያስነሱ፣ ሀገር ለማተራመስና ለማፍረስ ሆን ተብለው የሚሰራጩ፣ የማህበረሰቡን ለዘመናት ተከባብሮ የመኖር ሀገራዊ እሴቶችን ሆነ ብሎ ለማጥፋት የሚውተረተሩ አሉ

በአገራችን ባለው አሁነኛ እውነታ ግን ህዝብን በህዝብ ላይ የሚያስነሱ፣ አገር ለማተራመስና ለማፍረስ ሆን ተብለው የሚሰራጩ፣ የማህበረሰቡን ለዘመናት ተከባብሮ የመኖር አገራዊ እሴቶችን ሆነ ብሎ ለማጥፋት የሚውተረተሩ አሉ።

"አንድ አይና በአፈር አይጫወትም" እንደሚባለው፤ ያለችን አንድ አገር ናት። ይቺን አገር ደግሞ የተሻለች፣ ለዜጎቿ ምቹ፣ የበለጸገች፣ የተከበረችና የታፈረች የምናደርጋት እኛው ልጆቿ ነን። ይህንን ለማድረግ ሁላችንም ወቅቱ የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል መክሊታችንን አውቀን በመክሊታችን ልንሠማራ ይገባል። ከዚህ በተቃርኖም የጦርነት አውድማ፣ ሰላም የራቃት ሲኦል ልናደርጋት የምንችለውም እኛው ነን።

ይህንን በሌላ ምሳሌ ለማስረዳት ልሞክር፤ ኢትዮጵያን እንደ ፍጥረታዊ አካላችን እናስባት። እጅ፣ እግር፣ አፍንጫ፣ ዐይን፣ ጥርስ፣ ጉበት፣ ሳንባ፣ ወዘተ. የአንድ ሰው፤ ሰው የመሆኑ መዋቅሮች እና ንዑስ አካላት ናቸው። እነዚህ አካላት የተበታተኑና በየራሳቸው ሕልውና ያላቸው ቅርንጫፎች አይደሉም።

አንድ ላይ ሲሆኑ ዋናውን አካል ወይም ሰውየውን ህያው ፍጡር ያደርጉታል። ነገር ግን አይን የእግርን ሥራ ልሥራ፤ እግር ደግሞ የአይንን ሥራ ልተካ ቢል የሚሆን አይደለም። ልንቀሳቀስ ቢል እንኳን ፍጻሜው ሁለንተናዊ ጥፋት ነው የሚሆነው።

ምክንያቱም የዐይን ተግባር ማየት እና ለአዕምሮ ክፍላችንን የዕይታውን መረጃ ማቀበል ነው፤ እግርም ከዐዕምሮ በሚደርሰው ትዕዛዝ መሰረት የሰውዬውን አካል ይዞ ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ ነው፡፡ ነገር ግን ዐይን በእግር ቦታ ተተክቼ ልሥራ፤ እግርም በአይን ቦታ ተተክቼ ልሥራ፤ ወይም የራሴንም የሌላውንም ተግባር ልከውን ቢል አይቻለውም፡፡

ዐይን እግር ሆኖ አይራመድም፤ እግርም ዐይን ሆኖ አያይም፡፡ በአንድ አገር ያሉ ሕዝቦችም መክሊታቸው እንዲሁ ነው፡፡ ሁሉም በመክሊታቸው ሊተጉ እንጂ ያለ መክሊታቸው ገብተው ያልሆኑትን ሆነው ለመገኘት መሞከር የለባቸውም፡፡ ይህ ከሆነ እንደ አገር የሚፈለገው ብልጽግና ቀርቶ የማይፈለገው ምስቅልቅል ነው የሚፈጠረው፡፡ ስለዚህ አገር እንደ አገር እንድትቀጥል "የቄሳርን ለቄሳር" መስጠት ያስፈልጋል።

በብዙ ነገር ከዓለም በፊት የነበርን ህዝብ እርስ በእርስ እየተጓተትን ዛሬ ላይ የዓለም ጭራ ለመሆን የበቃነው የቄሳርን ለቄሳር ብለን ሁላችንም በየመክሊታችን ባለመገኘታችን ነው። አንድ ሰው በሙያው ተሰማርቶ እና በተሰጠው መክሊት ተጠቅሞ ከሠራ ውጤታማ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። በአንጻሩ ያለሙያው ገብቶ ያለመክሊቱ ልሥራ ቢል ከትርፉ ኪሳራው ያመዝናል።

አሁን ላይ ያለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታም ይሄንን የሚገልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የፖለቲካ ተንታኝና አክቲቪስት ሆኗል። የራሱን ኃላፊነት ተገንዝቦ መሥራት ያልቻለ ሁሉ በሌላው ሥራ ገብቶ ሲያቦካ ውሎ ያድራል፡፡ እኔ ምን ተሰጥቶኝ ምን ሠራሁ ከማለት ይልቅ እከሌ ይሄን ማድረግ አልቻለም፤ እከሌ ይሄንን ማድረግ ሳይገባው አደረገ፤ እከሌ ከእከሌ ጋር እንዲህ አይነት ቦታ ተገኘ፤... የመሳሰሉ ወሬና አሉባልታዎች ላይ ተጠምዶ ይውላል፡፡

ይሄን መሰል የራስን ተግባር በወጉ እንኳን ተገንዝቦ ኃላፊነትን ሳይወጡ ወደሌሎች ጣት መጠቆም፤ በማይመለከት ጉዳይ ገብቶ ስምና ግብርን የማጠልሸት አካሄድ አገርና ህዝብን ወደተሻለ ምዕራፍ አያሸጋግርም። ይልቁንም መሥራት ያለብንን ሳንሠራ እና ኃላፊነታችንን ሳንወጣ በመቅረታችን ምክንያት መተኪያ የሌላትን አንድ አገራችንን በገዛ እጃችን እንድናጣ እሰጋለሁ።

ከዚህ የተነሳ የሁሉም ዜጎች የአፍ ማሟሻ እየሆነ የመጣውን የፖለቲካ ጉዳይ ለፖለቲካ ልሂቃን እና ለፖለቲከኞች ትቶ፤ ሁሉም በተሰጠው መክሊት በተሰማራበት መስክ ተግቶ በመሥራት አገሩ ወደ ብልጽግና ማማ የምታደርገውን ጉዞ እውን ማድረግ ይጠበቅበታል።

እዚህጋ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ፤ ፖለቲካው ለፖለቲከኞች ይተው ሲባል፤ ፖለቲካው ለፖለቲካው ያለ ተመልካችና ሃይ ባይ ተዋናዮች ብቻ ይተው ማለት፤ ወይም ዜጎች የአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ አያገባቸውም ማለት አይደለም።

ይልቁንም ፖለቲከኞች መረን እንዳይወጡ እና ፈር እንዳይስቱ የሰላና አስተማሪ ትችት መስጠት፣ አቅጣጫ ማሳየት ከህብረተሰቡ የሚጠበቅ ነው። በተመሳሳይም ፖለቲካኞች የፖለቲካውን መንገድ በወጉ ተገንዝበው እና የአገርንና ህዝቡን ተጨባጭ እውነትና መሻት አውቀው የተሻለ ነገር ለመፍጠር መትጋት ይኖርባቸዋል፡፡

ለዚህ ደግሞ እውቀት፣ ቁርጠኝነት፣ የዓላማ ጽናት፣ ለሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ራስን ማስገዛት፣ ከራስ ይልቅ የአገርን የነገ ብልጽግና እውን ማድረግን የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል፡፡

አገርን ወደ ከፍታ ከማውጣት ይልቅ ወደ ገደል ከሚያንሸራትቱ የሴራና የመጠላለፍ ኋላቀር የፖለቲካ ባህል መላቀቅ፤ በጋራ ቆሞ ስለ አገርና ሕዝብ ጥቅም መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም ፖለቲከኞች በመካከላቸው ያሉ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ አገርና ህዝብን ወደ ተሻለ ምዕራፍ የሚያሻግር የጋራ ዕራይ ሰንቀው በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል።

አገርን የሚያሻግረው፤ የሕዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጠው፤ የሚፈለገውን ብልጽግናም እውን የሚያደርገው ይሄው መክሊትን አውቆ መሥራት፤ ኃላፊነትን ተቀብሎ በብቃት መወጣት ነው፤ ያለመክሊትና ሙያ ገብቶ የሌሎችን ተግባር ከመንቀፍ ይልቅ ሁሉም የየራሱን የቤት ሥራ በውጤት መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

መንግሥትም ለዚህ አይነቱ አካሄድ ችግር የሚፈጥሩ አሠራሮችና በአተገባበር ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ፈትሾ ማረም፤ ከዚህ ባለፈ የሀሳብ ብዝሀነት እንዲጎለብት በማድረግ ለአገሪቱ የፖለቲካ እድገት የአንበሳውን ድርሻ ሊወጣ ይገባል። ይህ ሲሆን ነገ ላይ ተፈጥራ ለማየት የምንናፍቃት አገር ስለመፈጠሯ ጥርጣሪ አይገባንም።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## አምራቾችን ማስተሳሰር የቻለው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከኢትዮጵያ እና ከመላው ዓለም የተውጣጡ 130 የሚደርሱ አቅራቢዎችና ከሶስት ሺ በላይ የንግድ ጎብኚዎች የተሳተፉበት 5ኛው አግሮ ፉድ እና ፕላስት ፕሪንት ፓክ የንግድ ትርዒት በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ሰሞኑን ለሶስት ቀናት ተካሂዷል:: ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ትኩረቱን ያደረገው በግብርና፣ በምግብ ማቀነባበሪያ፣ በንጥረ ነገሮች፣ በህትመት እና በማሸጊያ ኢንዱስትሪዎች ላይ ነው:: የንግድ ትርዒቱ የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ ወቅታዊ የንግድ እድሎችን ለማወቅ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም መፍትሄዎችን ለማመላከት ትልቅ ዕድል መፍጠሩን የንግድ ትርዒቱ ተሳታፊ አምራችና አቅራቢዎች ተናግረዋል::

በንግድ ትርዒቱ ምርቶቻቸውን ይዘው ከቀረቡ አምራቾች መካከል ሚድሮክ ኩባንያ ከሚያስተዳድራቸው ኩባንያዎች አንዱ የሆነው ሆራይዘን ፕላንቴሽን ይገኝበታል:: የሆራይዘን ፕላንቴሽን የሽያጭ ክፍል ኃላፊ አቶ ይርጋ ብርሃኔ እንዳሉት፤ ሆራይዘን ፕላንቴሽን ቡናን እና ሌሎች ምርቶችን የሚያዘጋጅ ድርጅት ነው:: ድርጅቱ እሴት የተጨመረበትን ተቆልቶ የተፈጨ ቡናን ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል::

ፕላንቴሽኑ በንግድ ትርዒቱ ላይ መገኘቱ ምርቶቹን ለማስተዋወቅ መሆኑን አቶ ይርጋ፤ አመላክተዋል:: ሆራይዘን ፕላንቴሽን ወደ ውጭ ከሚልከው ደረጃውን የጠበቀና ተቆልቶ የተፈጨ ቡና በተጨማሪ በአገር ውስጥ ገበያ ትላልቅ ሆቴሎችና ሱፐርማርኬቶች ላይ ሰፊ ተደራሽነት ያለው መሆኑንም ጠቁመዋል::

ዓለም አቀፍ በሆኑ የንግድ ትርዒቶች ላይ መሳተፍ ምርትን ከማስተዋወቅ ባለፈ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚናገሩት አቶ ይርጋ፤ ለአብነትም ሆራይዘን ፕላንቴሽን እሴት ጨምሮ የሚያዘጋጀውን ቡና ከሚፈልጉ ሆቴሎችና ሱፐርማርኬቶች እንዲሁም የውጭ ገዢዎች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችለዋል ይላሉ:: ለተዘጋጁ ምርቶች ማሸጊያ (ፓኬጅ) ከሚያዘጋጁ ድርጅቶች ጋር የመተዋወቅ ዕድል ይፈጥርለታል ሲሉም ገልጸዋል:: ይህም በዓለም ዙሪያ የገበያ ትስስር ከመፍጠር አልፎ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለሥራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ለልምድ ልውውጥ ትልቅ በር የሚከፍት ነው ብለዋል።

ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ምግብና ምግብ ነክ በሆኑ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደረገ እንደመሆኑ ምርት ፈላጊው ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር አምራች ኢንዱስትሪዎችም ማሸጊያ (ፓኬጅ) ከሚያመርቱ አምራቾች ጋር የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ:: በተለይም በአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲህ ያለ መድረክ እጅግ ያስፈልጋል:: አሁን ላይ ለሆራይዘን ምርቶች ማሸጊያ (ፓኬጂ) ድርጅቱ ማሸጊያዎችን ከዱባይ እንደሚያስመጣ ጠቅሰው፣ በአገር ውስጥም ማሸጊያ ፓኬጆችን የሚያመርቱ አምራች ድርጅቶች እንዳሉም ገልጸዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ለቡና ማሸጊያ በተለይም ወደ ውጭ ለሚላከው ቡና የሚጠቀሙት ማሸጊያ (ፓኬጅ) ከዱባይ የሚመጣ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከአገር ውስጥ አምራቾች ይገዛሉ:: ድርጅቱ በተለይም የሚድሮክ እህት ኩባንያ ከሆኑ በተለያዩ ኩባንያዎች የሚመረቱ እንደ ሻይ ቅጠል፣ ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ ለመሳሰሉ ምርቶች አገር ውስጥ የሚዘጋጀውን ማሸጊያ (ፓኬጅ) ይጠቀማል:: በመድረኩም በአገር ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ማሸጊያ (ፓኬጅ) አምራች ከሆኑ ኢንዱስትሪዎች ጋር የመተዋወቅና የገበያ ትስስር የመፍጠር አጋጣሚን የሚፈጥርላቸው እንደሆነ አመላክተዋል::

ሌላኛው ምርት አቅራቢ ድርጅት ኢኮ ግሪን ነው:: ድርጅቱ የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ይዞ ነው በንግድ ትርኢቱ ላይ የቀረበው:: የኢኮ ግሪን ድርጅት የማርኬቲንግ ባለሙያ አቶ ታዘበ ከበደ እንዳሉት፤ የኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ማዳበሪያ መቶ በመቶ የተፈጥሮ ነው:: የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያው ቀድሞ የሚታወቀውን ዩሪያና ዳፕን ተክቶ የሚያገለግል ሲሆን ኢኮ ግሪን ፈሳሽ ማዳበሪያው በፈሳሽ መልክ ሰብሉ ላይ የሚረጭ በመሆኑ ዩሪያና ዳፕ ተብሎ ከሚታወቀው ማዳበሪያ የሚለይ እንደሆነ ነው የተናገሩት::

ድርጅቱ ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን ወደ ገበያ ይዞ ከመጣ ከአስር ዓመታት በላይ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ታዘበ፤ ምርቱን ለማምረት የእንስሳትና የእጽዋት ተዋጽኦን የሚጠቀም እንደሆነ ነው የተናገሩት:: ማዳበሪያው ሙሉ ለሙሉ ተፈጥሯዊ በሆኑ በአገር ውስጥ ግብዓቶች የሚመረት ሲሆን፣ ድርጅቱም በቀን እስከ 100 ሺ ሊትር ማዳበሪያ የማምረት አቅም አለው::

ማዳበሪያው መቶ በመቶ ተፈጥሯዊ በመሆኑ በጊዜ ሂደት የአፈር ለምነትን እየመለሰ የሚመጣ ስለመሆኑ አቶ ታዘበ ጠቅሰው፤ ድርጅቱ ተሸላሚ እንደሆነም ተናግረዋል:: ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ እየሆነ እንደሚገኝም ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩ ምርቱን እንዴትና መቼ መጠቀም እንዳለበት የድርጅቱ ባለሙያዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ታች ላለው አርሶ አደር ጭምር እንደሚያስገነዝቡ አመልክተዋል:: አጠቃቀሙ ልዩነት ያለው መሆኑን ሲያስረዱም መሬቱ ከታረሰና ዘር ከተዘራ በኋላ ምርቱ ብቅ ማለት ሲጀምር የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያው እንደሚረጭ አቶ ታዘበ ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት:: በንግድ ትርዒቱ ላይ በርካታ ኩባንያዎችና ትላልቅ የእርሻ መሬት ያላቸው አምራቾች ተሳትፈዋል:: ከእነዚህ አምራቾች ጋር በቀላሉ መገናኘትና የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችላል:: በንግድ ትርዒቱ የተሳተፉ የተለያዩ አካላትን የመተዋወቅና የልምድ ልውውጥ እንዲሁም ተሞክሮን ማስፋት የሚያስችል መድረክ መሆኑን ጠቅሰው፣ ዘርፈ ብዙ ከሆነው አበርክቶው ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ ነው የተናገሩት::

በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የአፈር ማዳበሪያ መተካት የቻለው ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ አገሪቷ ያለባትን የውጭ ምንዛሪ ችግር በተወሰነ መጠን ማቃለል እንደቻለም ተናግረዋል:: ድርጅቱ በቀጣይም ሥራውን በማስፋት የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያውን ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል:: ምርቱ ከሰባት ዓመት በላይ ጥናትና ምርምር የተደረገበት መሆኑን ጠቅሰው፣ አሁን ተጨማሪ ጥናቶች በደብረብርሃን እና በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እየተደረጉ መሆናቸውንም ነው ያስረዱት:: ጥናቶቹ ሲጠናቀቁም የሚገኘው ውጤት ግብርናው ላይ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ነው ብለዋል::

ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ከአፈር ማዳበሪያ የተሻለ ዋጋ ያለው ስለመሆኑ የጠቀሱት አቶ ታዘበ፤ በኩባንያው ዋጋ በሊትር 60 ብር እንደሚሸጥም አስታውቀዋል:: አያይዘውም የግብርና ምርት እንደመሆኑ ጥንቃቄ ይፈልጋል ሲሉ ምርቱን እንደማንኛውም ሸቀጥ በማንኛውም ሱቅ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸው፣ በተለያዩ ዩኒየኖች፣ ማህበራትና በሌሎች ማዕከላት አማካኝነት አርሶ አደሩ ማዳበሪያውን ማግኘት እየቻለ ስለመሆኑም ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ምርቱን ለመጠቀም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል:: ለአብነትም ቅጠላቸው ሰፋፊ የሆኑ እንደ ጎመን አይነት ሰብሎች የሚጠቀሙት የማዳበሪያ መጠን ትንሽ መሆን አለበት:: ምክንያቱም መሬት የሚወድቀው ጠብታ በጣም ትንሽ ነው:: እንደ ጤፍ አይነት ትናንሽ የሆኑ ሰብሎች ደግሞ ሰፋ ያለ ርጭት ይፈልጋሉ:: ይህም አብዛኛው ርጭት መሬት የሚወድቅ በመሆኑ ነው::

አብዛኞቹ የአፈር ማዳበሪያዎች ኬሚካል ስለመሆናቸው የጠቀሱት አቶ ታዘበ፤ ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በመሆኑ የአፈር ለምነትን እየመለሰ በጊዜ ብዛት መሬቱ ወደ ተፈጥሮ ቦታው እንዲመለስ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረው፣ ዩሪያና ዳፕ ግን የአፈር ለምነትን እየቀነሰ እንደሚሄድም ገልጸዋል::

ሌላው ትላልቅ ማሽነሪዎችን ይዞ የቀረበው የቱርክ ኩባንያ ነው:: 32 ዓመታት ልምድ ያለው ኩባንያው በንግድ ትርዒቱ የተለያዩ ግዙፍ ማሽነሪዎችን ይዞ ስለመቅረቡ የኩባንያው ተወካይ ወጣት አክሱማዊት ዓባይ ትገልጻለች:: ተወካይዋ ኩባንያው ከፍተኛ ልምድ እንዳለው ጠቅሳ፣ መፍጫ ማሽነሪዎችን ወደ አገር ውስጥ እንደሚያስመጣም ጠቁማለች::

እሷ እንዳለችው፤ ወደ አገር ውስጥ ከሚያስመጣቸው ማሽነሪዎች መካከልም የስንዴ፣ የበቆሎና የጤፍ መፍጫ ማሽኖች ይገኙበታል:: ከዚህ በተጨማሪም የእንስሳት መኖ የሚዘጋጅበትን ማሽንም ያስመጣል:: ኩባንያው ማሽነሪ ከማስመጣት ባለፈ ሰዎች ማሽነሪውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ስልጠና ይሰጣል::

ኩባንያው አገር ውስጥ ካቀረባቸው ትላልቅ ማሽነሪዎች ተጠቃሚዎች መካከል ካኦ ጂጂ እና ዲኤች ገዳ ይገኙበታል:: ኩባንያው ለእነዚህ ድርጅቶች ማሽነሪዎቹን ከማስረከብ ጀምሮ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ስልጠና በመስጠት ጭምር ምርትና አገልግሎታቸውን አስተዋውቋል:: በዚህም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ ተችሏል ትላለች::

ቱርኮች የሚያመርቷቸው ማሽነሪዎች ጥራት እንዳላቸው የምትገልጸው አክሱማዊት፤ በእንዲህ አይነት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ መሳተፍ ደግሞ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንደሚረዳም ጠቁማለች:: አምራች ኢንዱስትሪዎች ለምርታቸው የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎችን ማስመጣት የሚችሉት ዓለም አቀፍ በሆኑ ኤግዚቢሽኖች ላይ በሚፈጠር የገበያ ትስስር እንደሆነም ጠቁማለች::

በኤግዚቢሽኑም ቱርክን ጨምሮ የቻይና፣ የኩዌትና የሌሎች አገራት ኩባንያዎችን መመልከት ችለናል:: የአገር ውስጥ አምራቾች ከእነዚህ ኩባንያዎች የሚፈልጓቸውን ምርቶች ከማግኘት ባለፈ የገበያ ትስስር መፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የሚችሉ ሲሆን፤ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ከንግድ ትርዒቱ ማግኘት እንደሚችሉም ከተሳታፊዎች መረዳት ችለናል::

በንግድ ትርዒቱ የመክፈቻ መርሃ ግብር ላይ የተገኙት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ሃሰን መሐመድ እንዳሉት፤ የንግድ ትርዒቱ በዓለም ዙሪያ የገበያ ትስስር ከመፍጠር አልፎ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለሥራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ለልምድ ልውውጥ ትልቅ በር ይከፍታል። በተለይም በኢትዮጵያ ሶስት አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ስራ መግባታቸው ከተለያዩ የዓለም አገራት የተውጣጡ ኢንቨስተሮች ወደ አገሪቱ እንዲገቡ ማድረግ አስችሏል። እነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮችም በአማራ ክልል ቡሬ፣ በኦሮሚያ ክልል ቡልቡላ፣ በሲዳማ ክልል ይርጋለም የሚገኙ ናቸው::

ፓርኮቹን በታቀደው ልክ መጠቀም እንደሚገባ ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመው፤ የአገሪቱን ምርቶች በጥሬያቸው ወደ ውጭ ገበያ ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ በመላክ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተሻለ መልኩ መገንባት እንደሚቻል ነው ያመላከቱት::

የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ከ280 ሺ አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር እንደቻሉ የገለጹት አቶ ሃሰን፤ የሥራ እድል ፈጠራውንም ከ40 ሺህ በላይ ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከግብርና ከኢንዱስትሪ እና ከንግድ ጋር ተሳስረው በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ዓለም አቀፍ አምራቾችን እንዲሁም ኢንቨስተሮችን ወደ አገር ውስጥ መሳብ ተችሏል:: በዚህም ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተጠናከሩ ይገኛሉ:: መንግሥትም በእነዚህ ዘርፎች ምቹ አካባቢ እና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል::

በተለይም ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በተመለከተ አምስት ክላስተሮችን በማዋቀር ኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ለውጥ እየመጣ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በግብርና፣ በምግብ ማቀነባበሪያ፣ በንጥረ ነገሮች፣ በህትመት እና በማሸጊያ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮረው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትም የዚህ ውጤት አንዱ ማሳያ መሆኑን አስታውቀዋል::

ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ለገበያ ትስስር፣ ወቅታዊ የንግድ እድሎችን ለማወቅ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና መፍትሄዎችን ለማመላከት ትልቅ እድል የሚፈጥር እንደሆነ ተመላክቷል::



የንግድ ትርዒቱ በተጎበኘበት ወቅት

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሚዲያዎች የሕዝብ ናቸውን?

**ዋስልኝ አየለ**

የብዙ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች መሪ ቃል፤ የሕዝብ ልሳን፣ የሕዝብ ድምጽ፣ የሕዝብ ዓይንና ጆሮ... በአጠቃላይ የሕዝብ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው:: ለመሆኑ ግን የሕዝብ ሲባል ምን ማለት ይሆን?

የሕዝብ የሚባለው ነገር ብዙ ጊዜ ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር ነው የሚያያዘው:: በተቃውሞም ሆነ በድጋፍ በኩል ያሉት ሚዲያዎች የሕዝብ ነን የሚሉት በፖለቲካዊ ጉዳዮች ነው:: መንግሥትን ከልክ በላይ ማወደስ ወይም 24 ሰዓት መንግሥትን ብቻ መውቀስ ማለት ነው:: በዚህ መሐል የሕዝብ ጉዳዮች ሽፋን ሳያገኙ ተዳፍነው ይቀራሉ::

የሕዝብ ሲባል፤ የሕዝቡ የዕለት ከዕለት የሕይወት እንቅስቃሴ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ትውፊታዊ ልማድ፣ የሚዝናናበትንና ብሶቱን የሚገልጽባቸውን ስሜቶች ማጋራት፣ ወቅታዊ የሥራ እንቅስቃሴዎቹን አጀንዳ ማድረግ የመሳሰሉት ብዙም ትኩረት አይሰጣቸውም:: ከግማሽ በላይ የሚሆነው የአገራችን የኅብረተሰብ ክፍል አርሶና አርብቶ አደር ነው:: ከዚህ የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ የአገሪቱን መሪ እንኳን የማያውቅ ይኖራል:: በእርግጥ የማሳወቅ ሥራ ነው መሠራት ያለበት:: ዳሩ ግን አቅራቢያው ያለውን ነገር በመተው አይደለም::

ለምሳሌ፤ አሁን ወሩ የሰኔ ወር ነው:: የሰኔ ወር ማለት በአገራችን የወቅቶች ምደባ የክረምት ወር መጀመሪያ ነው:: ‹‹ሰነፍ ገበሬ በሰኔ ይሞታል›› የሚባል አባባል አለው ገበሬው:: ዋናው የኑሮው መሠረት የሆነው የግብርና ሥራ የሚሠራው በሰኔ ነው:: በሰኔ ያልተዘራ ዘር ወቅቱ ስለሚያልፍበት ምርታማ አይሆንም:: ስለዚህ በዚህ ወቅት ለገበሬው ከምንም በላይ አንገብጋቢው ጉዳይ ስለግብርና ሲወራለት ነው:: ጆሮውን ሰጥቶ፣ ልቡን ከፍቶ የሚያዳምጥ ስለግብርና ሲወራለት ነው:: የሚዝናናው እንኳን ስለግብርና ሲወራለት ነው::

እዚህ ላይ አንድ የራሴን ትዝታ ላንሳ:: የ10ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ተፈትኜ ውጤት እየተጠባበቅኩ በነበረበት ወቅት የነሐሴ ወር ከገባ ጀምሮ የሬዲዮ ዜና የማዳምጥ በተመስጦ ነበር:: ልክ ‹‹የ10ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና...›› ሲል ሰውነቴ ሁሉ ጆሮ ይሆናል:: የፈተናውን ዜና ከሰማሁ በኋላ እንኳን ደጋግሞ እሱ ብቻ ቢወራ እወዳለሁ:: በወቅቱ ሌሎች ዜናዎች ምንም ስሜት አይሰጡኝም:: ይህ ልጅነት ነው እንበል፤ ዳሩ ግን በየትኛውም ዕድሜ ላይ ብንሆን ስለሚቀርበን ነገር ሲወራልን ነው የምንወድ::

ለመሆኑ ሚዲያዎቻችን ምን ያህል የሕዝብ ናቸው? ዜናዎቻቸውም ሆነ ፕሮግራሞቻቸው ለተወሰነው (የተማረ ለሚባለው) የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ አይደለም ወይ? ይህ የሚሆነው ደግሞ የግል (የንግድ) በሆኑት ብቻ ቢሆን ኖሮ ብዙም አይደንቅም ነበር:: የሕዝብ ናቸው በሚባሉት (ተጠሪነታቸው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለክልል/ከተማ አስዳደር ምክር ቤት) የሆኑት ሁሉ ናቸው:: አርሶና አርብቶ አደሩን የሚመለከቱ ፕሮግራሞች አሉ ቢባል እንኳን በሚመለከተው ተቋም የተገዙ የአየር ሰዓቶች ናቸው:: ያ የአየር ሰዓት የዚያ ተቋም ነው::

ዜናዎች ወይም ፕሮግራሞች የሚሠሩት በብዛት ሁነት ተጠብቆ ነው:: ለምሳሌ፤ ገበሬዎች ተቃውሞ ካሰሙ፣ መንግሥት መልዕክት ካስተላለፈ፣ የድርቅ ወይም የጎርፍ አደጋ ሲያጋጥም ነው:: ከዚያ ውጭ በመደበኛነት የብዙ የኅብረተሰብ ክፍል ሕይወት ነው ተብሎ የሚሠራበት በጣም ጥቂት ነው:: ከፖለቲካዊ ጉዳዮች አንፃር ሲታይ እዚህ ግባ አይባልም::

በሁሉም ደረጃ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል (የተማረ፣ ገበሬ፣ ነጋዴ...) እኩል የሚያስደስት ዜና ወይም ፕሮግራም ላይኖር ይችላል:: ግን የገበሬው ሕይወት የማይመለከተው አለ ወይ? ሐኪም ወይም መሐንዲስ ወይም መምህር ወይም ነጋዴ ‹‹ኤጭ! የግብርና ወሬ አስጠላኝ!›› ብሎ ያውቃል? በየትኛውም የሙያ ዘርፍ ውስጥ ያለ የተማረ የሚባል ሰው የገጠሩ ማኅበረሰብ ላይ የሚሠራ ፕሮግራም አስጠላኝ (ሰለቸኝ) ብሎ አያውቅም:: ችግሩ የሚዲያ ሰዎች ስንፍና ብቻ ነው::

ከሦስት ይሁን አራት ዓመት በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ የግብርና ሚኒስቴር በአዳማ ከተማ የሰጠው አንድ ሥልጠና ላይ ተሳትፌ ነበር:: ብዙ ሰዎች የሰጡት አስተያየት ‹‹ለምንድነው ግብርና ላይ እንደ ሌላው ጉዳይ በሰፊው የማይሠራው?›› የሚል ነበር:: ከመድረክ የተሰጠው መልስ ጋዜጠኞች ላይ ስንፍና እንዳለ የሚጠቁም ነበር:: የገጠሩን ሕይወት ለማሳየት ድካም አለው:: ጭቃ ወይም ዝናብ አለ፤ አቧራ ወይም ፀሐይ አለ:: መንገዱ ምቹ አይደለም፤ ውጣ ውረድ አለው:: መኝታውም ሆነ ምግቡ ከተማ ቦታ እንደተለመደው አይደለም:: በእነዚህ ምክንያቶች የመሥራት ተነሳሽነቱ ብዙም የለም:: ይህ ችግር ግን ከጋዜጠኛው ብቻ ሳይሆን ከአመራር ጀምሮ የሚፈጠር ነው::

ይህ ሲባል ግን የሚመሰገኑ የሉም ማለት አይደለም:: ለምሳሌ፤ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለዓመታት የዘለቀው (እኔ እንኳን ሳውቀው ከ6 ዓመት በላይ ሆኖታል) ‹‹ውሎ አዳር›› ፕሮግራም የገጠሩ ብቻ ሳይሆን ከተሜው እንኳን የወደደው ፕሮግራም ነው:: ፕሮግራሙ የሚተላለፈው የገጠሩ ማኅበረሰብ እረፍት በሚሆንበት እሁድ ቀን ነው::

ከግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ‹‹ባላገሩ›› ቴሌቪዥን ላይ የአርሶ አደሮች የጥያቄና መልስ ፕሮግራም አለ:: አዘጋጁ (ማሩ ባላገሩ) ልክ እነርሱን መስሎ ነው የሚያቀርበው:: አርሶ አደሮችን በማዝናናት ያስተምራል ማለት ነው::

አማራ ቴሌቪዥን ላይ ለዓመታት የዘለቀው የአርሶ አደሮች ወግ አለ:: ይህ ፕሮግራም የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽንን የገጠሩ ሕዝብ እንዲያየው ከሚያደርጉ ፕሮግራሞች ዋናው ሳይሆን አይቀርም::

እነዚህን ፕሮግራሞች እንደ ምሳሌ ያመጣኋቸው ለመተቸት ብቻ ሳይሆን የተወደዱ ፕሮግራሞች ሲኖሩ ማድነቅም እንዳለ ለማሳየት ነው:: ምክንያቱም የከተማው ነዋሪ ሁሉ ነው የወደደላቸው:: ስለዚህ ሀገረሰባዊ ፕሮግራሞችን መሥራት ምን ያህል ተወዳጅ እንደሚያስደርግ ከእነዚህ ማየት ይቻላል ማለት ነው::፡

ሥራው አድካሚ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም:: ብዙ አካላዊ ድካም አለበት:: ዳሩ ግን የሕዝብ ነን ከተባለ ደግሞ ሕዝቡን መምሰል የግድ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የከተሜው ብቻ አይደለም፤ ሲቀጥል ደግሞ የከተሜው ሕዝብ የገጠር ፕሮግራም አታሳዩኝ አላለም:: እንዲያውም ከገጠሩ ማኅበረሰብ ያላነሰ ነው የሚወደው:: ሌላውንማ ከየትኛውም አማራጭ ያገኘዋል:: የዓመቱን የግራሚ እና ኦስካር ሽልማቶች፣ የቢልቦርድ መረጃዎች በየትኛውም አማራጭ ያገኛል:: ማየት የሚፈልገው የበይነ መረቡ ዓለም የማያውቃቸውን የአገሩን ቱባ ባሕሎችና ሥርዓተ ክዋኔዎች ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የአገራችን ቱባ ባሕሎችና ሥርዓተ ክዋኔዎች፣ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናዎች ወደ በይነ መረቡ ዓለም መግባት አለባቸው::

የመዝናኛ ፕሮግራሞቻችን የግድ የውጭ ሰርከስ ብቻ መሆን የለባቸውም:: የገጠር ልጆች ሐረግ ላይ የሚያደርጉት ዥዋዥዌም ጨዋታ ነው:: የፈረንጆች የመሸዋወድ (ፕራንክ ይሉታል) ጨዋታ ብቻ አይደለም የሚያዝናና፤ የአገር ቤት ሰዎች ወግ ያዝናናል:: የአገር ቤት የባህል ዘፈኖችም ያዝናናሉ:: የሳልሳ ዳንስ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔሮች ጭፈራዎችም ያዝናናሉ:: የኦሮሞ ቆነጃጅት አንገታቸው የተቀጨ እስከሚመስለን ድረስ ያንን ፀጉራቸውን ሲያዞሩት ጭፈራ ብቻ ሳይሆን ሰርከስም ሆኖ ያዝናናል:: የትግራይ ቆነጃጅት ሲሽከረከሩ ማየት፣ የጎጃም እንቅጥቅጥ ማየት ከሳልሳ ያንሳል ወይ?

በአጠቃላይ ሚዲያዎቻችን የሕዝብ ነን ካሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይምሰሉ!

# ዓለም አቀፍ



## ኔቶ ሩሲያን ለማስጠንቀቅ ያለመ የጦር ልምምድ ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኔቶ ሩሲያን ለማስጠንቀቅ ያለመ የጦር አውሮፕላኖች ልምምድ ማድረግ መጀመሩን አስታወቀ::

በጀርመን አስተባባሪነት የሚካሄደው የኔቶ የጦር አውሮፕላኖች ልምምድ ለአንድ ሳምንት ይቆያል ተብሏል::

የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ጦር ወይም ኔቶ የአየር ላይ ውጊያ ልምምድ ማድረግ የጀመረው ጦርነት ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገራት ሊስፋፋ ይችላል የሚል ስጋት ስለገባው መሆኑ ተገልጿል::

“የአየር መከላከል 23” የሚል ስያሜ የተሰጠው ይህ የአውሮፓ አገራት የውጊያ አውሮፕላኖች የጋራ ልምምድ ከ250 በላይ የጦር አውሮፕላኖች እንደሚሳተፉበት ዩሮ ኒውስ ዘግቧል:: በልምምዱ ላይ 25 የኔቶ አባል አገራት እየተሳተፉ መሆኑ የተነገረ ሲሆን ከ10 ሺህ በላይ ወታደሮችም እንደሚሳተፉበት በዘገባው ላይ ተጠቅሷል::

በልምምዱ ላይ ከኔቶ አባል አገራት በተጨማሪ የጃፓን እና ስዊድን የጦር አውሮፕላኖች ይሳተፋሉም ተብሏል:: የጦር ልምምዱ በተለይም የሰው አልባ እና የክሩዝ ሚሳኤል ጥቃቶችን ማክሸፍ በሚቻልበት መንገድ እንደሚያተኩር ነው የተገለጸው::

ከዩክሬን ጋር እየተዋጋች ያለችው ሩሲያ በቀጣይ ሌሎች አገራትን ልታጠቃ ትችላለች የሚል ስጋት ያለው ኔቶ፥ የአባል አገራቱ ስንዝር መሬት ጥቃት እንዳይደርስበት ለመጠበቅ ሁሌም ዝግጁ መሆኑንም አስታውቋል::

በጀርመን የአሜሪካ አምባሳደር ለዩሮ ኒውስ እንዳሉት የኔቶ አባል አገራት የጋራ ልምምድ ለሩሲያ መልዕክት ለማስተላለፍ ያለመ ነው:: የኔቶ የአየር ላይ ውጊያ ልምምድ በአውሮፓ የሚደረጉ መደበኛ የበረራ አገልግሎቶችን ሊያስተጓጉል እንደሚችል ተሰግቷል ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው::

## ሳውዲ አረቢያ ከቻይና ጋር የበለጠ
## መተባበር እንደምትፈልግ ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሳውዲ አረቢያ ከቻይና ጋር የበለጠ መተባበር እንደምትፈልግ ገለጸች::

ሳውዲ አረቢያ ከምንግዜም ተቀናቃኟ ኢራን ጋር በቻይና አደራዳሪነት ወደ ስምምነት የመጣች ሲሆን ከቤጂንግ ጋር ያላትን ግንኙነት የበለጠ ማጥበቅ እንደምትፈልግ አስታውቃለች::

የሳውዲ አረቢያ የሃይል ሚኒስትር ለቪኦኤ እንዳሉት ከቻይና ጋር መወዳደር ሳይሆን የትብብር አጀንዳዎችን ማጠናከር የሪያድ ፍላጎት ነው ብለዋል:: ሪያድ ግንኙነቷን ከቻይና ጋር ማጥበቋን ተከትሎ ከምዕራባውያን አገራት የመጠራጠር ስሜት እያደገ ነው ያሉት ሚኒስትሩ ይህ ግን ሳውዲን አያሳስብም ማለታቸው ተገልጿል::

የዓለማችን ቀዳሚ ነዳጅ ሻጭ አገር የሆነችው ሳውዲ አረቢያ ነዳጅን በመሸመት ከዓለም አገራት መካከል ቀዳሚ ከሆነችው ቻይና ጋር ከንግድ ባለፈ በብዙ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል:: ሁለቱ አገራት በተለይም በጸጥታ እና ደህንነት ጉዳዮችም በጋራ ለመስራት ከስምምነት ላይ የደረሱ ሲሆን ቻይናን በጠላትነት የፈረጁት ምዕራባውያን አገራት የአገራቱን ግንኙነት በመጠራጠር ላይ ናቸው ተብሏል::

የሳውዲ አረቢያ የሃይል ሚኒስትር ልዑል አብዱል አዚዝ ቢን ሳልማን በዚህ ጉዳይ ላይ በተጠየቁበት ወቅት እንዳሉት ለምዕራባውያን መጠራጠር ምላሽ የለንም፣ ቢዝነስ ቆሞ አይጠብቅህም ቢዝነሱ ወዳለበት በነጻነት እንንቀሳቀሳለን ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል::

"የምዕራባውያን አገራት ከእኛ ጋር ናችሁ ወይስ ከማን ጋር ናችሁ እያሉ ይጠይቁናል” የሚሉት ሚኒስትሩ ሪያድ ከማንኛውም አገር ጋር ጥቅሟን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ትመሰርታለች ሲሉም አክለዋል:: ቻይና የሳውዲ አረቢያ ዋነኛ ነዳጅ ገዢ አገር ስትሆን ሁለቱ አገራት በዩዋን ለመገበያየትም መስማማታቸው ተገልጿል::

ሚኒስትሩ አክለውም የቻይና የነዳጅ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል፣ ይህን ፍላጎት ደግሞ እኛ ለመሙላት እየሞከርን ነው እኛ ከማንም አገር ጋር እየተፎካከርን አይደለም ብለዋል::



**የሳውዲ አረቢያ የኃይል ሚኒስትር ልዑል አብዱል አዚዝ ቢን ሳልማን**

# ባለውለታዎቻችን

## የመጀመሪያው ሲቪሉ የመከላከያ ሚኒስትር

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ስህተትን ለማረም፣ ለማስተካከል፣ ራሳችንን ለማነጽ ስንፈልግ ቅድሚያ የምንፈልጋቸው የቀደሙትን ባለውለታዎቻችንን እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም:: ምክንያቱም እነርሱ ዘንድ ታሪክ አለ፤ በእነእርሱ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ድል፣ ተስፋና ፍቅርም አለ:: ለሌሎች መኖርና ሌሎችን ማቆምም እንዲሁ ስንፈልግ ከእነርሱ ጋር የምናገኘው ነገር ነው::

በእነርሱ ቀጣዩን ትውልድ በመልካም ስነምግባር ይታነጻል፤ በመልካም ጎዳና ይመራል:: ምክንያቱም ሕይወታቸው መምህርም መሪም ነው:: አርኣያነታቸው መንገድ ጠራጊ ነው:: እነርሱ ጋር እውቀትና ልምድን፣ ማስረጃንና በቂ መረጃን ማግኘትም ይቻላል:: ያንን ይዞ ደግሞ በአመክንዮና በምክንያት ሂስ መስጠት ይቻላሉ:: ምክንያቱም ሀሳባቸው ምጡቅና ተቀባይነት ያለው ነው::

እነርሱ ጋር ለአገር መሥራትና ለአገር መሞት እንዲሁም የአገር ፍቅር ዘላለማዊ ነው:: ስለዚህም በዚህ ውጣውረዳቸው ታሪካቸውን አስቀምጠው ለሌሎች መማሪያ ገድል ሆነዋል:: ተቀባይ ከሆንን፤ እኛም ታሪክ ሰሪ እንድንሆን አቅጣጫን ጠቁመውናል:: እነዚህና መሰል ባህሪያትን ከተላበሱት መካከል ለዛሬ ‹‹የባለውለታዎቻችን›› አምድ እንግዳ ያደረግንላችሁ አንጋፋ ዲፕሎማት ናቸው:: እኚህ ባለውለታችን የቀድሞው የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር ሲሆኑ፤ አያሌው ማንደፍሮ ይባላሉ::

አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ የተወለዱት ከአባታቸው ከአቶ ማንደፍሮ ኃይለጊዮርጊስ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ አየለ ግንቦት 27 ቀን 1927 ዓ.ም (እ.ኤ.አ June 4, 1935) በሐረር ከተማ ነው። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በሐረር ከተማ በሚገኘው በራስ መኮንን ትምህርት ቤት ገብተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት መከታተል ችለዋል።

የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ደግሞ የተከታተሉት በቀድሞው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነው:: የተመረቁበት የትምህርት መስክ ምኅንድስና ሲሆን፤ ቀጥለው ደግሞ ወደ ውጪው ዓለም በማምራት ሌላኛውን የከፍተኛ ትምህርት በአሜሪካን አገር ታፍት ዩኒቨርሲቲ ቦስተን ማሳቹሴት ሲሆን፤ በኢንተርናሽናል ግንኙነት ተመርቀዋል።

በ1950 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1958) ወደ እናት አገራቸው ተመልሰው በኢትዮጵያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ አሜሪካን ክፍል ተመድበው ሥራ የጀመሩት አምባሳደር አያሌው፤ በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የልጅ ሚካኤል እምሩ ልዩ ጸሐፊ ሆነው አገልግለዋል። ቀጥሎም ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው በመሾማቸው፤ የእርሳቸው የቅርብ ረዳትና አማካሪ በመሆን ለዓመታት በሙሉ ታማኝነት ሰርተዋል:: በእርግጥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲገቡ መጀመሪያ በረዳት ሚኒስትርነት በኋላም በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ የአሜሪካንን ክፍል ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል።

ከአቶ ከተማ ጋር በነበራቸው ወዳጅነትና የቅርብ ግንኙነት በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ተሰሚነታቸው በጉልህ የሚታይበት ወቅት እንደነበርም ታሪካቸው ያስረዳል። ይህ ከሚኒስትሩ ጋር ያላቸው ቅርርበት ደግሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረቱ ላይ አሻራቸውን እንዲያኖሩ አግዟቸዋል:: ማለትም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከመመስረቱ በፊት የአፍሪካ መሪዎችና መንግስታት ለድርጅቱ መመስረት ድጋፋቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው የዲፕሎማሲ ጥረት ትልቅ ጉዞ በየዋና ከተሞቹ በማከናወን ውጤታማ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ነበር::

ከሚኒስትሩ ጋር በጣምራ አያሌ የአፍሪካ መሪዎች ዘንድ የግርማዊ ጃንሆይን መልዕክቶች በማቅረብና በየግላቸው በማነጋገር እንዲሁም በማግባባት

**በ1957 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1965) አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ መጀመሪያ በረዳት ሚኒስትርነት ቆየት ብሎ ደግሞ በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ የአሜሪካንን ክፍል ከመሩ በኋላ ደግሞ በ1963 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1971) የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሶማሊያ ተሹመው በዚያድባሬ ዘመነ መንግስት የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማሻሻል እንዲሰሩ ተደርገዋል**



አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ

የፈጸሙት ሚናም ዘላለም የሚረሳ እንዳልሆነም የህይወት ታሪካቸው ያወሳል። በዚያኑ ዘመን አፍሪካ በካዛብላንካና በሞንሮቪያ ቡድኖች በመከፋፈሏ አዲስ አበባ ላይ ሁሉንም ያካተተ ስብሰባ ለማካሄድ አስቸጋሪ በሆነበት ወቅት የአምባሳደር አያሌውና ሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ድርሻ ላቅ ያለ ነበር::

በዲፕሎማሲው ዘመቻ ታላቁን ኃላፊነት ወስደው በመስራታቸው ታላቅ አክብሮት እንዲሰጣቸው እና ባለታሪክ ሆነው እንዲታወሱ አስችሏቸዋል። በተጨማሪ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመመስረቻ ቻርተር በሚዘጋጅበት ጊዜ አምባሳደር አያሌው በማቀነባበርም ሆነ ባበረከቱት ሃሳብ ሥራው እንዲጣደፍ ማድረጋቸውም ይነገራል። ስብሰባው በተከናወነበት ጊዜም ቢሆን ለሊት እና ቀን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የኮንፈረንሱን ጽህፈት ቤት ተግባር በኃላፊነት ከፈጸሙት መካከልም ስማቸው ይጠራል።

በሴኔጋል ዳካር ከተማ በመጀመሪያው የአፍሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ የድርጅቱ ዋና መቀመጫ የት ከተማ እንዲሆን በሚከራከርበት ጊዜ አምባሳደር አያሌው ከኢትዮጵያውያን መልዕክተኞች መካከል ንቁ ተሳታፊ በመሆን ከዳካር ከተማ ይልቅ አዲስ አበባ የድርጅቱ ዋና መቀመጫ ሆና እንድትመረጥ ካስቻሉት ውስጥ ግንባር ቀደም ናቸው:: ካይሮ ላይ በ1964 ዓ.ም በተደረገው የመሪዎች ጉባዔ በፀደቀው ውሳኔ አዲስ አበባ የአፍሪካ መቀመጫ እንድትሆንም አሻራቸውን ያሳረፉ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል።

በ1957 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1965) አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ መጀመሪያ በረዳት ሚኒስቴርነት ቆየት ብሎ ደግሞ በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ የአሜሪካንን ክፍል ከመሩ በኋላ ደግሞ በ1963 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1971) የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሶማሊያ ተሹመው በዚያድባሬ ዘመነ መንግስት የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማሻሻል እንዲሰሩ ተደርገዋል::

በውጤታማ ተግባራቸውም ብዙ አስደሳች ለውጦችን ማምጣት ችለዋል:: ለአብነት የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት አፄ ኃይለሥላሴ በአምባሳደር አያሌው ጉትጎታና ተደጋጋሚ ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞቃድሾን እንዲጎበኙ ሆኗል። ይህ ደግሞ በጉብኝታቸው የተመኙትን ያህል ውጤት ባያገኙም ሁለቱን መሪዎች በቀጥታ ማነጋገር መቻላቸው ተስፋ ጫሪ ሥራ ነበር:: ምክንያቱም በወቅቱ የሁለቱን መንግስታት የአቋም ልዩነት በጣም ሰፊ ነበር:: እናም በእርሳቸው ሥራ ልዩነቶቹ መቀነስ እንደቻሉ ታሪካቸው ይናገራል።

በሞቃዲሾ በአምባሳደርነት በቆዩበት ወቅት አምባሳደር አያሌው ሌላም ሥራ ሰርተዋል:: በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረውን ውጥረት ማብረድ የቻሉ ሲሆን፤ በተለይም ከጦርነት አፋፍ ላይ የነበሩበትን ሁኔታ ማቅለል ችለዋል። ከሞቃዲሾ ወደ ሐረርጌ ደጋግመው በመመላለስ ሶስተኛውን ክፍለ ጦር በሚጎበኙበት ጊዜ አምባሳደር አያሌው የሰሩትም ተግባር ዛሬ ድረስ የሚታወሱበት ነው:: የሶማሌን መንግስት የመስፋፋት ፖሊሲና የትጥቅና የጦር ዝግጅት ላይ ሙሉ መረጃ በማካፈልም በኢትዮጵያ በኩል ያለውን ጉድለት በግልፅ በመወያየት የሞራል ድጋፍ ለሰራዊቱ አድርገዋል::

የንጉሠ ነገሥቱ መንግስት ሥርዓት በአብዮቱ ተገርስሶ ደርግ ስልጣኑን በያዘበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ መከላከያ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ሲቪሉ አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ ሲሆኑ፤ የጦር ሰራዊቱ በሞቃዲሾ አምባሳደር በነበሩበት ጊዜ ያሳዩትን ትጋትና የአገር ፍቅር በመገንዘቡ ለዚህ ሹመት መብቃታቸው ይነገራል።

አምባሳደር አያሌው በመከላከያ ሚኒስትርነት ዘመናቸው የሶማሌ የጦር ኃይል ለወረራ መዘጋጀቱን በማወቃቸው ለኢትዮጵያ ጦር መሳሪያ ለማግኘት አያሌ መንግስታት ዘንድ በመልዕክተኝነት ተዘዋውረው ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት በብርቱ የጣሩ ባለውለታ እንደሆኑም ታሪካቸው ይናገራል።

ሌላው አምባሳደር አያሌው የሰሩት ተግባር በሱማሊያ ጠረፍ የተከሰተውን አስጊ ሁኔታ እየባሰ በሄደበት ወቅት ያደረጉት ነገር ነው:: ይህም ከምዕራብ ዓለም ጋር ደርግ የሚተሳሰርበትንና አቅም የሚፈጥርበትን ሁኔታ ማመቻቸታቸው ሲሆን፤ በተለይም በፖለቲካ፣ በመሳሪያ ድጋፍና መሰል ነገሮች አጋር ይሆናሉ ያሏቸውን ሁሉ እንዲጠቀሙ ከአገሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያሻሽሉ በምክር ደግፈዋል:: በዚህም ምክንያት ከ30 ወራት ኩርፊያ በኋላ የደርግ መንግስት አምባሳደር አያሌውን አምባሳደር በማድረግ ዋሽንግተን እንዲሰሩ ሾሟቸዋል። ግን ከአሜሪካን ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የማይደግፉ ወገኖች አምባሳደሩ አዲስ አበባን በመልቀቂያቸው ዋዜማ የግድያ ሙከራ አድርገውባቸው በተአምር ከአደጋ እንደተረፉ በታሪካቸው ላይ ተቀምጧል።

ዋሽንግተን ገብተው ለጥቂት ወራት ሥራቸውን እንደጀመሩ ከደርግ መንግስት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየሻከረ የሄደው አምባሳደር አያሌው፤ በግንቦት ወር 1970 (እ.ኤ.አ June, 1978) ዓ.ም ሥራቸውን ለመልቀቅ ወስነዋል:: መልቀቅ እንደሚፈልጉም አሳውቀው ተሰናብተዋል:: በዚህም በቨርጂንያ አሌክሳንድሪያ ከተማ በስደት ኖረዋል:: ነገር ግን በዚያ ሳሉ ዝም ብለው አልተቀመጡም:: ለኤመርሰንና ለኮሞሳት በተባሉ ኩባንያዎች ውስጥ ለመሥራት አመለከቱ:: በኃላፊነትም ለዓመታት ሰሩ:: እንዲያውም በምክትል ፕሬዚዳንትነት እስከ ጡረታ እድሜያቸው ድረስ አገልግለዋል::

አምባሳደር አያሌው ረቂቅ እና አስደናቂ ባህሪ ነበራቸው:: በዋሽንግተን ዲሲ በስደት በኖሩበት ወቅት የዳያስፖራው መናኸሪያ ኮከብ የነበሩ ሲሆን፤ የአፍሪካ ሶሳይቲ መስራች መሆናቸውም ይነገራል::

አምባሳደር አያሌው ሌላም ሊያስጠራቸው የሚችል ገድል የፈጸሙ ሲሆን፤ ይህም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርነት ባገለገሉባቸው ዓመታት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ከባልደረቦቻቸው ጋር የጎላ ሚና ተጫውተዋል::

አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ በመከላከያ ሚኒስቴር በሥራ ላይ እያሉ ከወይዘሮ ፀዳለ ከበደ ጋር የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ሁለት ልጆች ያፈሩ ሲሆን፤ ልጆቻቸውም ዶክተር ምህረት ማንደፍሮ እና ልጅ ሙሴ ማንደፍሮ ይባላሉ:: አያት መሆን የቻሉት እኚህ ባለውለታ፤ ዞሮዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከሞት አይቀርምና እርሳቸውም ታሪክ ተክለው በደረሰባቸው የአንድ ሳምንት ሕመም ሐምሌ 26 ቀን 2011 ዓ.ም. በ84 ዓመታቸው በአሜሪካን ፌርፋክስ ሆስፒታል ሕይወታቸው አልፏል:: መልካም እረፍትን ለላይኛው ቤታቸው ተመኘን:: ሰላም!!

# ስፖርት

## ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የእጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ ቻምፒዮን ሆነ

**አስማየሁ ግዛው**

የ2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፕሪሚየር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አሸናፊነት ተጠናቀቀ:: ክለቡ የኢትዮጵያ የእጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ ቻምፒዮና በመሆን የዋንጫ እና የወርቅ ሜዳልያ ተሸላሚ ሆኗል።

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ 7ኛ ዓመት የ2015 ዓ.ም የክለቦች ፕሪሚየር ሊግ የማጠቃለያ ውድድር በአዲስ አበባ ትንሿ ስቴድየም በጠንካራ ፉክክሮች ታጅቦ ፍሜውን አግኝቷል:: ሁለተኛ ዙር የእጅ ኳስ የክለቦች ፕሪሚየር ሊግ የማጠቃለያ ውድድር ከ15ኛ እስከ 18ኛ ሳምንት ከግንቦት 26- ሰኔ 3/ 2015 ዓ.ም ጠንካራ ፉክክሮችን ያስተናገደ ሲሆን ቂርቆስ ክፍለ ከተማ አጠቃላይ አሸናፊ መሆን ችሏል።

የማጠቃለያ ውድድሩ በአንድ ሳምንት ገደማ ቆይታው ባስተናገዳቸው ውድድሮች የሊጉን ዋንጫ ለማንሳት ጠንካራ ፉክክሮች ተስተናግዷል:: የፕሪሚየር ሊጉ ክለቦች ያሳዩት ጠንካራ ፉክክር ማን ቻምፒዮን ይሆናል የሚለውን እስከ ሊጉ ፍጻሜ ድረስ በጉጉት እንዲጠበቅ አድርጎት ቆይቷል። ክለቦቹ ያሳዩት የተፎካካሪነት ደረጃ እጅግ ማራኪና አጓጊ ነበር።

ስምንት ክለቦችን ለአንድ ዓመት ሲያፋልም የቆየው የእጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ መቻል፣ አሜድላ፣ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ፣ ፌደራል ማረሚያ ቤት፣ ከምባታ ዱራሜ፣ ባህርዳር ከነማ እና ፋሲል ከነማ ጠንካራ ፉክክር አድርገውበታል። በመጨረሻም ሊጉን ዋንጫ በማንሳት ልምድ ያካበተው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ በ30 ነጥብ ከማቻል ጋር እኩል ሆኖ በጎል ክፍያ ብቻ በመብለጥ ቻምፒዮንነቱን አረጋግጧል። መቻልን



**ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ለ4ኛ ጊዜ የእግ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫን አንስቷል፣**

ተከትሎም ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ እጅ ኳስ ክለብ ሶስተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቅ ችሏል::

ቂርቆስ ክፍለ ከተማ እጅ ኳስ ክለብ መቻልን ከመሳሰሉ ጠንካራ ተፎካካሪዎች የገጠመውን እልህ አስጨራሽ ፉክክር በድል በመወጣት የተዘጋጀውን የዋንጫና የወርቅ ሜዳለያ ከክብር እንግዶች ተቀብሏል:: ክለቡ ሊጉን ከተቀላቀለ ስድስት ዓመታትን ብቻ ቢያስቆጥርም ለተከታታይ 4 ጊዜያት ቻምፒዮን በመሆን ትልቅ ታሪክ ጽፏል:: በዘንድሮው ውድድር ዋንጫውን ከፍ ከማድረጉም በተጨማሪ ኮከብ አሰልጣኝና ኮከብ ተጨዋቾችም ማስመረጥ ችሏል።

የቻምፒዮኑ እጅ ኳስ ክለብ ዋና አሰልጣኝ አቶ ሙሉጌታ ግርማ ኮከብ አሰልጣኝ ተብለው በመመረጣቸውና ክለባቸው ቻምፒዮን በመሆኑ መደሰታቸውን ገልፀው፣ የክለቡ ስኬት ታዳጊ ፕሮጀክቶች ላይ ጠንካራ ስራ በመስራቱና ተተኪ ስፖርተኞችን በየጊዜው ማፍራት በመቻሉ መሆኑን ተናግረዋል። አቶ ሙልጌታ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች ለክለቡ የሚያደርጉት ድጋፍ በዋናነት ክለቡን በተከታታይ ዓመታት ቻምፒዮን እንዲሆን እንዳስቻለውም አስረድተዋል። የእጅ ኳስ ክለቡ ተጫዋቾችም ድካማቸው በቻምፒዮንነት መፈፀሙ እንዳስደሰታቸው ገልፀውም በቀጣይ የክፍለ ከተማው አስተዳደር የክለቡን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

የክፍለ ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጠብቀው አመሸ በበኩላቸው፣ የእጅ ኳስ ክለቡ የበለጠ ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል እንደ ከዚህ ቀደሙ የበጀት እና ሙያዊ ድጋፍ እንዲሁም መሰረታዊ ነገሮች ለማሟላት ጥረት እንደሚደረግ ቃል ገብተዋል።

በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት የዘንድሮውን የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ ለክለቡ ባስረከቡበት ወቅት፣ ክለቡ ከአገር አልፎ በአፍሪካ ኢትዮጵያን በመወከል እየተወዳደረ ያለ እንደመሆኑ ሊመሰገንና ሊበረታታ እንደሚገባው ተናግረዋል።

የቂርቆስ የእጅ ኳስ ክለብ ኢትዮጵያን በመወከል በአፍሪካ የእጅ ኳስ ክለቦች ቻምፒዮና ውድድር ላይ በተከታታይ ዓመታት መሳተፍ የቻለ ሲሆን በቅርቡም በግብፅ በተካሄደው የአፍሪካ የእጅ ኳስ ቻምፒዮና ውድድር ላይ ተሳትፎ የሚያበረታታ ውጤት በማስመዝገብ ተመልሷል። የፕሪሚየር ሊጉ ቻምፒዮን ክለብ በአፍሪካ ደረጃ በሚካሄዱት የክለቦች ቻምፒዮና ውድድሮች ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ ዘንድሮም የሚቀጥል ይሆናል::